ክፍል ሁለት

(፪)

ጣማፍ ኄራኒ፥ የገነት ዕንቁ፤ ገዳማዊት መብራት።

Tamav Eren The Jewel of Heaven &

The Beacon of Monasticism.

መግቢያ

ክርስቲያኖች የሥጋ ሞትን እንደ ዳግም ልደት ይቈጥሩታል። እንዲሁም እንደ ቅብጥ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓት፤ የመነኰሳትና መነኰሳይያት ዕለተ ሞታቸው (በሥጋ)፤ ዓለሙን ሁሉ ንቀው ምንኵስና የተቀበሉበት ዕለት ነው። ለመመንኰስ ከሚፈጸምላ ቸው ሥርዓተ ጸሎት ውስጥ፥ የፍትሓት ጸሎትም ይገኝበታል።[1] ከዚህ ሥርዓት በኋላ፥ የመነኰሴ ወይም የመነኰሲት አንድነታቸው፤ ከዓለማውያኑ ጋር ሳይሆን፥ ከእግዚ አብሔርና ከቅዱሳኑ ጋር ብቻ ነው። የእናት ኄራኒ የምንኵስና ሕይወትም በ፲፱፻፶ ዎቹ ማለቂያ ላይ በዚህ ሁኔታ ነበር የተወጠነው።

«የእስራኤል አምላክ ተናገረኝ፥ የእስራኤል ጠባቂ እንዲህ አለ፦ በሰው ላይ በጽድቅ የሚሰለ ጥን በእግዚአብሔርም ፍርሓት የሚነግሥ፥ እንደ ማለዳ ብርሃን እንደ ፀሓይ አወጣጥ፥ በጥዋትም ያለ ደመና እንደሚደምቅ ከዝናብ ብኋላ ከምድር እንደሚበቅል ልምላሜ ይሆናል» (፪ኛ ሳሙ.፳፫፥፫-፬)። የእናታችን እማሆይ ጣማፍ[2] ኄራኒ የሕይወት ታሪክ፥ ብርሃኑን ለሚያበራልን ለመንፈስ ቅዱስ፥ ውዳሴና ስግደት እናቀርብ ዘንድ ይጋብዘናል።

ጣማፍ በሕይወት ዘመኗ የፈጸመችው አገልግሎትና ተጋድሎ በመለኮት ፈቃድ የሆነ ነው። ያለ ፈቃደ እግዚአብሔር የሚሆን ነገር የለምና። ፈተናዎችን ሁሉ በጽኑ እምነት በመታገልና መስቀሏን በመሸከም፤ በቅዱስ መንበሩ ፊት፥ በፍቅር የሞላ መልካም መሥዋዕት አቅርባለች። በብርሃናዊ ሕይወቷ በፈጸመቻቸው ምግባራ ትና በጠቅላላው በመልካም አርኣያነቷም ሰማያዊ ክብርን ወርሳለች።

በተመስጠ ሆነን የኣገልግሎቷን ስፋት ስናስበው፥ የጐሰቈለችውንና በፈተና ውስጥ ያለችውን ቤተ ክርስቲያናችንን ያጸኑ ዘንድ፤ ገባሬ ኩሉ የሆነ አምላካችን፥ እር ሷንና ሌሎችንም እንደ እርሷ ያሉትን ዐምዶች፥ የሰጠን መሆኑን እንረዳለን። እመ ትጉሓን የሆነች እናታችን ኄራኒ፥ በድንግልና ለመኖር ቃል ከገባችበት ጊዜ አንሥቶ፥ እስከ ዕለተ ዕረፍቷ ድረስ በፈጸመቻቸው ታላላቅ ምግባራት፤ ገዳማት ዳግም እንዲጠ ነክሩና የመንፈስ ብርሃናቸውን ዳግም እንዲያገኙ እንዲፈነጥቁትም አድርጋለች።

ይህ የተቀደሰ የሕይወት ታሪኳ፥ ምድራዊ የንጽሕና ሕይወትን መልካምነት ያሳያል። የእርስዋ ሕይወት፥ ገዳማዊነትን በትክክል ያሳየ ሰማያዊ ሰው ወይም ምድራዊ መልኣክ የሚያሰኝ ነው። የጥንታውያኑን ገዳማውያን አበውና እማት ኣኗኗር እን ድናይ አድርጋናለች። ሥርዓቱን በሕይወቷ እያሳየች ወይም እየኖረችው፥ አዲሱ ትውል ዳችን የጥንታውያኑን ቅዱሳን መጽሓፍ ቅዱሳዊ ሕይወትና፤ ሕግጋተ እግዚአብሔር እንዴት መጠበቅ እንዳለበት እንዲረዳ አድርጋለች። ስለ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት

[1] {በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንም እንዲሁ ነው።}

[2] {በቅብጥ እናቴ ወይም እናታችን ማለት ነው። በብዛት የምትጠራው ግን፥ ኡምና ኄራኒ ተብላ ነው።}

እውነተኛነትና፣ ስለ እግዚአብሔር ክብር የሚታይ፣ የሚዳሰስ ምሳሌም ሆና አልፋ ለች። «የእግዚአብሔር ከተማ ሆይ፥ በአንቺ የተከበረ ነገር ይባላል» (መዝ. ፹፮/፹፯፫)።

ጣማፍ ከልደት እስከ ዕረፍቷ ያሳለፈችውን ሙሉ ሕይወት እንጻፈው ብንል፥ በዚህ አንስተኛ መጽሓፍ ሊጠቃለል አይችልም። ስለዚህ ዋና ዋና የምንለውን ብቻ፥ በየ ርዕሱ ከፋፍለን አቅርበናል። በዚህ በሁለተኛው መጽሓፍ የምናቀርበው፥ ስለ ጌራኒ የልጅነት ሕይወትና፣ ለልጆቻቸው መልካም አርአያ ስለሆኑት፥ ትጉሓን ወላጆቿ ነው። ለዚህ የተቀደሰ ሕይወቷ፣ መሠረቱን ስለ ጣለላት ወንድ አያቷ፥ ማቴዎስ አል-ፈዚ (Matta Al-Feazi) እና የእናቷ እኅት የሆነች የአክስቷ ሞፌዳን አስተዋጽኦ እና ቀርባለን።

የለጋዋን ችግኝ አስተዳደግና፣ በጽኑ ዐላማና በቆራጥነት ለገዳማዊ ፍሬ መብ ቃቷን፥ በታላቅ አክብሮትና ደስታ ልናየው ይገባናል። ይህም በአ.ሰ.ሴ.ገ. በምትኖር አንዲት ወጣት መነኲሲት አማካይነት፣ ሰማያዊ መልእክት እስኪደርሳት ድረስ ያለ ውን መንፈሳዊ ሕይወቷን የሚያስነብበን ነው።

ስለ ጽኑ እምነቷና ቅንነቷ፥ እግዚአብሔር በታላቁ ሰማዕት ቅዱስ መርቆሬ ዎስ (አቡ ሰይፊን[3]) አማካይነት፣ በራእይ ወደ ገዳሙ እንድትሄድና እንድትሳለም አድርጎ፥ ወደ ቤቱ ጠርቷታል። በዚህ መጽሓፍ፥ እግዚአብሔርን እያመሰገንን በላሮ ጌዋ ካይሮ ወደሚገኘው የአ.ሰ.ሴ.ገ. አገባቧንና የምንኩስና ሥርዓት አፈጻጸሟን፣ እን ዲሁም በዚህ ሂደት ውስጥ ያለፈችበትን ውስብስብ መንገድ እናስነብባለን። ይህን ገድ ሏን መዝግበን ለማቆየት የምንሻው፣ አሁን ላለው ትውልድ ብቻ ሳይሆን፥ ለመጪ ውም ትውልድ መማሪያና መመሪያ ይሆን ዘንድ በመመኘት ነው። «ስለ ሃይማኖቱና ስለ የዋህነቱም ቀደሰው፣ ከሰውም ሁሉ እርሱን መረጠው» (ሲራ.ክ.፵፭፥፬)።

የልቧ ንጽሕና፣ ለሰዎች የምታሳየው አክብሮት፣ ራሷን ዝቅ ማድረጓ፣ መል ካም ራእይዋ፣ እያንዳንዱ እንቅስቃሴዋና ንግግሯ ኢየሱስ ክርስቶስን ይሰብካል። ከሃ ገር ውጪም በሃገር ውስጥም ያለና ይህን ምግባሯን ያየ ወይም ድምጿን የሰማ ሁሉ፣ በመንፈስ ቅዱስ ጎይል ወደ እግዚአብሔር ፍቅር ይቀርባል። ሁሉን በፍቅር የሚቀበል ፈጣሪም ወደ ቤቱ ያስገባቸዋል። በዚህም እግዚአብሔር ይወደሳል፣ ይመሰገናል።

ራሷን ዝቅ ስለ ማድረጓና ስለ ትሕትናዋም ብዙዎች ተማርከዋል። ብዙዎ ችም መስክረውላታል። እግዚአብሔር ድክመቷንና ታናሽነቷን ተመልክቶ ብቻ፣ ክብ ሩን በእርሷ እንደሚገልጥ እንጂ፥ ከእርሷ የሆነ አንዳች ነገር እንደሌለ በንጹሕ ልብና አንደበት ትነግራቸዋለች። ሊያወድሳት ወይም ምስጋና ሊያቀርብላት የሚያስብ ሰው ካለ፥ በፍቅሩ የያዘንን የሰማዩን አምላካችንን አመስግኑ፥ በማለት ራሷን ከውዳሴ ከንቱ

[3] {የሁለት ሰይፎች አባት ማለት ነው። የሰማዕቱ ታሪክ (ገድል) በዝክረ ቅዱሳን ዘተዋሕዶ አንደኛ መጽሓፍ/ አዜብ በርሄ/ አዲስ አበባ/ (በ፳፻ ዓ.ም. እትም ገጽ ፳፰፣ በ፳፻፲፭ ዓ.ም. እትም ገጽ ፴) ላይ ይገኛል።}

ታሸሽለች። ይህ ሁሉ የሚያሳየው፥ ከማያልቅ ጸጋው አብዝቶ እንደሰጣትና፣ እርሷም ይህንን ጥሪቷን (መክሊቷን) በግብርም በቃልም ለሁሉ እንደምታካፍል ነው። እግዚ አብሔር አምላካችን እርሱ እምነትም ብርሃንም ነውና፣ እርሷም በእውነቱ ውስጥ የምትኖር በብርሃኑም የበራች ናትና፣ እናታችን ጌራኒ ቡርክት ናት!!

ምንም እንኳን የኣመራር ኀላፊነቱን ተቀብላ፣ ገዳሙን በእመምኔትነት እንድ ታገለግል ፈቃደ እግዚአብሔር ቢሆንም፣ እርሷ ግን ከዚህ ኀላፊነት ለመሸሽ ያላደረገ ችው ሙከራ አልነበረም። ነገር ግን ፈቃደ እግዚአብሔር ተፈጽሞ፣ ኀላፊነቱን በግድ ከተቀበለች በኋላ፥ የገዳሙን ድክመት ለማስተካከልና፣ ለአ.ሰ.ሴ.ገ. ብቻ ሳይሆን የግብ ፅን ገዳማት ሥርዓት የቀየሩ፥ በርካታ ታላላቅ ሥራዎችን ለመሥራት ወዲያው ታጥቃ ተነሣች።

ይህን ታላቅነቷን በደንብ የተረዳነው የምድራዊ ሕይወቷ ፍጻሜ አካባቢ ነው። ቍጥር በሌለው የበሽታ ዐይነቶች ተሠቃይታ፣ ጕስቍላና አካሏ ዝሎ ሳለ፥ በመንፈስ ግን እጅግ ጠንካራና ወደ ሰማይ ምጡቅ ሆና፣ ተአምራት ታደርግና ወደ ፊት ስለሚፈጸሙ ነገሮችም ትተነብይ ነበር። መከራ መስቀሏ ወይም የሰማዕትነት ገድሏም፥ ዐይነቱ ብዙ የሆነ ሕመመሟ ነው።

የተከበራችሁ የዚህ መጽሓፍ አንባብያንና አንባብያት፥ ይህ በዚህ መጽሓፍ የጻፍነው የቅድስና ታሪክና ተአምር፣ ያለምንም ማጋነን የተዘገበ ነው። ነገር ግን፥ ከእናታችን ጣማፍ ጌራኒ ጋር አብረን ኖረን፥ ንጹሓን እጆቿ የሠሩትን አይተናልና «. . . የምናውቀውን እንናገራለን፣ ያየነውንም እንመሰክራለን . . .» እንዲል፥ እርሷም ተአም ሯና ቅድስናዋ ሊነገር ይገባልና፥ በእርሷ ምክንያት ለእግዚአብሔር ምስጋና ማቅረብ ተገቢ ስለሆነም የምስክርነት ቃላችንን አስተላልፈናል (ዮሐ.ይ፥፲፭)።

ያም ሆኖ ግን፥ አሁን እኛ በዓይናችን ካየነውና ከእንደበቷ ከሰማነው ለማቅ ረብ ያደረግነው ሙከራ፣ ከቅድስና ባሕር ላይ አንድ ጠብታ የመውሰድ ያህል ነው። ይህ መጽሓፍ ሥራዋን በሙሉ ይናገራል ባንልም (ሁሉን እንጻፈው ብንልም ስለማ ንችል)፣ እግዚአብሔር ለቅዱሳኑ በሚያደርገው ቸርነት ሊመሰገን ይገባዋልና የቻልነ ውን ያሕል ብቻ ልንጽፍ ተገደናል። «የመንግሥትን ምሥጢር ሊሰውሩት፥ የእግዚአብሔርን ሥራ ግን በክብር ሊገልጡት ይገባልና፣ መከራም እንዳታገኛችሁ በጎ ሥራን ሥሩት» (ጦቢት ፲፪፥፯)።

እናታችን ጌራኒ ሁሌም ትመኝልን እንደ ነበረው፣ የክብሩ ወራሽ እንሆን ዘንድ፣ በእርሷ ጸሎትና ምልጃ አማካይነት እግዚአብሔር እንዲረዳን ምኞታችን ነው። በእ ርሷ ሕይወት ውስጥ፥ በግልጽ ይታይ የነበረውን ቅድስና ይሰጠንና በመንገዱም ይመ ራን ዘንድ፣ በእርሷ አርአያነት ያኖረንም ዘንድ፣ በእናቱ በቅድስተ ቅዱሳን ድንግል ማርያም፣ በታላቁ ሰማዕት አቡ ሰይፊን አማላጅነትና በብፁዕ ወቅዱስ አባታችን አቡነ

ኒኑዳ ፫ኛ ጸሎት ይርዳን። ለብፁዕ ወቅዱስ አባታችንም ረጅም ዕድሜና ጤና ይስጥ
ልን። ለዘለዓለሙ አሜን።

የታላቁ ሰማዕት የአቡ ሰይፊን ገዳም አገልጋይ መነኰሳይያት ልጆቿ።
ኅዳር ፴ ቀን ፲፱፻፶፱ ዓ.ም. (30 Hatour 1723)።

የመጽሐፉ አዘጋጆች በብዙ ቦታዎች ላይ ስለ ኡምና ጌራኒ ሲናገሩና ሲያወድ
ሷት፣ እንደ ሦስተኛ ሰው ሳይሆን፥ አንቺ እያሉ ያቀረቡትን ጽሑፍ እኔ ለኣጻጻፍም
ይሁን ለንባብ አመቺ ይሆን ዘንድ፣ እርሷ እያልሁ በሦስተኛ ሰው አገባብ አቅርቤዋ
ለሁ። ለምሳሌ «በዚህ ሁሉ ውስጥ ያንቺ መልካም አርኣያነት አለ» የሚለውን፣
«በዚህ ሁሉ ውስጥ የእርሷ መልካም አርኣያነት አለ» ወደሚል በመቀየር ነው።

አብዛኛው የሕይወት ታሪኳና ገድሏ የቀረበው፣ እርሷ ራሷ ባደረገችላቸው
ትረካ ላይ የተመሠረተ በመሆኑና፣ አንዱ ርእስ ሌላውን እየሳበ ወደ ሌላ ትረካ ስለ
ሚወስዳትና ስለ ጥንቱም ስለ ኋለኛውም እየቀላቀለች ስለምትነግራቸው፥ በየርእሱ
ሥር ያለውን ታሪክ በተሰጠው ቦታ ብቻ ማጠቃለል እንዳይቻል አድርጎታል። ስለ
ዚህ በኣንድ ክፍል፣ ምዕራፍ ወይም ንዑስ ምዕራፍ ሥር ሊካተት የሚገባውን ታሪክ
ያለ ቦታው ማንበብ በብዙ ያጋጥማል። አንድ ምዕራፍ ላይ በዋና ታሪክነት የቀረበ
ውን ርእስ፥ ሌላ ምዕራፍ ላይ እንደ ማጠናከሪያ ሆኖ (ወይም ነገርን ነገር ስቦት)
ቀርቦ ሊገኝ ይችላል።

ተርጓሚዋ።

ምዕራፍ አንድ

ጣማፍ ጌራኒ[4] ያሳ ኼላ (Tamav Erene Yassa Khella)፦

ንጽሕተ ንጹሓን ቅድስተ ቅዱሳን የሆነች ድንግል እናታችን ወላዲተ አምላ
ክን አጋዥ አድርገን፤ ከተቀደሰ ቤተሰብ የወጣችና የተመረጠ መልካም ፍሬ የሆነች፤
የእናታችን የጣማፍ ጌራኒን ሕይወት፥ ከልደት እስከ እድገት እናቀርባለን።

ልደት፦ ሕፃን ፋውዜያ (Fawzya) (ጣማፍ ጌራኒ) ፍጹም ቅዱሳን ከሆኑ ቤተሰብ የካ
ቲት ፪ ቀን ፲፱፸፱ ዓ.ም. (Amshir 2, 1652 AM[5] «ዘመነ ሰማዕታት») ተወለደች። አባቷ
ያሳ ኼላ፣ እናቷ ጀኔፍየፍ ማታ አል-ፌዚ (Genevieve Matta al-Feazi) ይባላሉ። ወላ
ጆቿ ከቅዱሳኑ ጋር ጥሩ ወዳጅነት የነበራቸውና መልካም ሕይወት የሚመሩ፣ በምፅ
ዋትና በመሳሰሉት መንፈሳዊ ምግባራትም የሚሳተፉ ነበሩ። ልጆቻቸውንም በዚሁ
መንፈስ አበልጽገው አሳድገዋቸዋል። «ሁለቱም በጌታ ትእዛዝና ሕግጋት ሁሉ ያለ ነቀፋ እየ
ሄዱ፥ በእግዚአብሔር ፊት ጻድቃን ነበሩ» እንዲል (ሉቃ.፩፥፮)።

ከእነዚህ መልካም ፍሬዎች አንዷ የሆነችውና፤ እግዚአብሔር ከልደቷ ጀምሮ
የጠበቃትና አገልጋዩ ያደረጋት እናት (ኡምና) ጌራኒ ናት። ሕፃን ፈውዜያ በምትወ
ለድ ጊዜ፥ እናቷ የወሊድ ችግር ቢገጥማትም፥ ሐኪም ቤት ለመሄድ አልፈቀደችም።

ልጁ በምጥ ስትሰቃይ ያየውና የደኅንነቷ ጉዳይ ያሳሰበው፤ የጀኔፍየፍ አባት
አል-ፌዚ፥ ታሕታ (Tahta) ወደሚገኘው የቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ሄዶ፥ ልጁ
በሰላም እንድትገላገልና የልጁ ልጅም ጤነኛ ሆና ትወለድ ዘንድ፤ እግዚአብሔር እን
ዲረዳው እያለቀሰ ጸለየ። የሰማዕቱ የቅዱስ ጊዮርጊስንም አማላጅነት ተማጸነ። ጀኔፍየ
ፍም እያለቀሰች እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምን እየተማጸነች ነበር። በዚህ
ምጥና ጭንቀት ላይ እንዳለች፥ ቤቱ በኣንድ ጊዜ በብርሃን ሞላ። ከዚያም ቅድስት
ድንግል ማርያም፥ ቅዱስ ጊዮርጊስን አስከትላ ስትመጣ ታያት።

ቅዱስ ጊዮርጊስ ወደ እርሷ ቀርቦ፤ ጀርባዋን በእጆቹ ሦስት ጊዜ መታ መታ
አደረጋት። ወዲያው ቆንጆዋ ሴት ልጅ፥ ፋውዜያ ተወለደች። እመቤታችን ሕፃኗን
አንሥታ፥ አቀፈቻትና በትእምርተ መስቀል በገጿ ላይ ካማተበችባት በኋላ፥ ለእናቷ
መለሰችላት። ከዚያም «እርሷ የእኛ እንጂ፥ የኣንቺ ልጅ አይደለችም። በመልካም

---

[4] {መጽሐፈ ስንክሳር የጌራኒን ትርጉም «ሰላም፣ ፍቅር» ይለዋል። (ከመጋቢት - ጷግሜን፤ ት/ማ/ድ፤ አ/አ፤ ፲፱፸፫ ዓ.ም.፤ ገጽ ፭፻፲፪፤ ነሓሴ ፳፭ ቀን።)}

[5] «AM» -በቅብጥ ባሕረ ሐሳብ የዘመን አቈጣጠራቸው በ«ዘመነ ሰማዕታት» ሲሆን፥ የሚጀምረውም ንጉሥ ድዮ
ቅልጥያኖስ በሥልጣን ከኖረበት ዘመን ከ፪፻፹፭ ዓ.ም. ነው። በተለይ ከ፲፻፫-፲፻፰ ያለው ጊዜ የቅብጥ ክርስቲያ
ኖች በእጅጉ የተጨፈጨፉበትና አስከ ስምንት ሺህ ክርስቲያኖች ሰማዕት የሆኑበት ነው። ይህን ታላቅ የቤተ
ክርስቲያን መከራ ለማዘከር የዘመን አቈጣጠሩንም «ዘመነ ሰማዕታት (Anno Martyrorum)» ብለውታል።

የጸሎት ትምህርት ቤት፦ እንደዚህ በቅዱሳን ተከብባ ያደገችው ፋውዜያ፤ እናቷ ገና በጨቅላነቷ ነበር ነገረ እግዚአብሔርን ማስተማር የጀመረቻት። እራሷ ጣማፍ ጌራኒ ከልጅነት ትዝታዋ እንዲህ ስትል አጫውታናለች።

† *ስለ ጸሎትና ስግደት ጥቅም የተማርሁት ከእናቴ ነው። እርሷ የሰባቱን ሰዓታት ጸሎት* (Agpeya) *ሳታሰታጉል ትጸልይ ነበር። እኔም ታድያ በሕፃንነቴ ወደ ጸሎት ቤቷ ተሹለክልኬ እገባና፤ ከጎኗ ቆሜ የምታደርገውን አስተውላለሁ።*

እየደጋገመች መሬት ላይ ድፍት ብድግ ስትል (ስትሰግድ) ለመጀመሪያ ጊዜ ላይ፥ ደንግጬ አምርሬ አለቀስሁ። ስግደቷን አቋርጣ አቅፋ ካባበለችኝ በኋላ፥ «ለኢየሱስ ክርስቶስ ክብር ነው የምሰግደው» አለችኝ። ግን ለምን? ብዬ ሰጠይቃት፥ «እኔ እንደማደርገው አድርጊ» ብላ አሳየችኝና ስግደቷን ቀጠለች። እኔም አብሬያት መስገድ ጀመርሁ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ፥ በምታደርገው ረጅም ጸሎት አብሬያት መሆን ጀመርሁ። በዚህ ሁኔታ ሥጋን በስግደት ማድከም፣ ሕሊናን በጸሎት ወደ ሰማያት መሰቀል፤ እንዳይደመሰስ ሆኖ በልጅነት ዕድሜዬ በውስጤ ተቀረፃ ቀረ።

አንድ ጊዜ እንደማስታውሰው ደግሞ፥ በታኅሣሥ ወር በዚያ የብርድ ወቅት[7] ፤ እናቴ በመስኮት በኩል ቆማ፤ ወደ ቅዱስ ገዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ስትመለከት ሰላየ ኺት፥ እዚህ ለምን ቆምሽ? ብዬ ጠየቅኋት። ወንበር አምጥታ መስኮቱ አጠገብ አስቀመጠችና እዚያ ላይ አቆመችኝ። ከዚያም «ጸሎት አይሰማሽም?» አለችኝ። አወን ይሰማኛል ብያት፤ የጸሎቱን ሥርዓት (ሥርዓተ ቅዳሴ) ከመጀመሪያው እስከ ፍጻሜው አብረን ተከታተልን። ይህን ዐይነት ቅዳሴ በሌሊት ከአንድ ጊዜ በላይ አድምጠናል።

አንድ ቀን፥ እናቴ የአጥቢያውን ቄስ፤ ቅዳሴ ለምን በሌሊት እንደሚቀድሱ ጠየቀችው። እርሱም በሌሊት ቀድሰው እንደማያውቁ ነገራት። እርሷም ብዙ ጊዜ፥ በተመሳሳይ ሰዓት ሥርዓተ ጸሎትና ቅዳሴ እንደምትሰማ በእርግጠኝነት ስትነግረው፥ ግሑሳን[8] መሆን አለባቸው፥ አንቺ የታደልሽ! ከበረከታቸው ተሳታፊ ትሆኚ ዘንድ እግዚአብሔር ፈቅዶልሻል» አላት።

---

[7] {የኢትዮጵያ የበጋ ወራት፥ በግብፅ ክረምት ነው።}

[8] ግሑሳንና ግሑዳት (Sowah) አንዳንድ ጊዜ፥ እንደ ባሕታውያን ወይም መናንያን ይጠቀሳሉ። ሆኖም ይህ የተሳሳተ ግንዛቤ ነው። እነርሱ ከዚያም በላይ ናቸውና። ግሑሳን በመንፈስ የመጠቁ ናቸው። እነርሱ በላዮር ላይ ሲበሩና ከቦታ ቦታ ያለችግር ሊንቀሳቀሱ የሚችሉ ናቸው። (Jacques Lacarrière) ስለ እነርሱ እንዲህ ብሏል፦ «ይህ ጸጋ ያላቸው አባቶች፥ ከግብፅ ተነሥተው፥ በጣም በአጭር ጊዜ ውስጥ፥ ሮም ወይም ቢዛንታይን ይገኛሉ። ከዚያ ደግሞ ተመልሰው በበኣታቸው ይታያሉ። እነዚህን ከሰዎች ሁሉ ልዩ የሆኑ ቅዱሳን (Télékinésis) ይላቸዋል። ለእነዚህ ቅዱሳን እንደ ምሳሌ አድርጎ፤ በሯኛው ም.ዓ. የብዙ መነኮሳትና መነኮሳይያት መምህር የነበረውን፥ ሊቀ ካህናት አባ ሺኑዋን መጥቀስ ይቻላል። በዚህ ጸጋው ብዙ ድንቅ ነገሮች ማድረጉን፤ አባ ሞሳ (Wisa) የተባለ ደቀ መዝሙሩ ጽፏል። (The Life of Shenoute by Besa. Pp.57-61፤ ፩ኛ ነገ.፲፰፥፲፪)፤ {እንዲሁም በዚሁ መጽሐፍ ላይ ከፍል ፬፣ ምዕራፍ ፪ንይመልከቱ። ግሑሳን -ለወንድ ጸታ ለብዙ ቍጥር ሲሆን በነጠላ ቍጥር ግሑስ ይባላል። እንዲሁም ለእንስት በነጠላ ግሕስት፤ በብዙ ግሑሳት ነው።}

አስተዳደግ አሳድጊያት» አለቻት።

የቤተሰቡ አባላት በአዲሷ ሕፃን ደስተኞት ቢሆኑም፥ እናትና አባት ግን አንድ ስጋት አደረባቸው። ቅድስት ድንግል ማርያም «ልጅቷ የእኛ ናት» በማለቷ፤ ምክንያት ሕፃኗ በሞት እንዳትለያቸው ፈሩ። ከዚህ ስጋታቸው የተነሣ፥ ማንኛውንም ከሕፃኗ ጋር የተያያዘ ነገር ሁሉ፤ በታላቅ ጥንቃቄና ፍቅር ይፈጽሙ ጀመር። የክርስትናዋ ቀን ሲደርስ፥ ፋውዜያ ወደ ሊቀ ባሕታውያን አባ ሺኑጣ (ሲኑዳ) ገዳም ተወስዳ፤ የአካሚና ሱሓግ ሀ.ስ.ሊ.ጳ. በሆነው በአባ ጴጥሮስ (Boutris) (፲፱፻፫-፲፱፺፬) እጅ ተጠመቀች። አጥማቂው አባ ጴጥሮስ፥ ለወላጆቿ፤ «ልክ አጥምቄ ከገንዳው ሳወጣት፥ ይህ ገዳም በስሙ የተገደመለት፥ አባ ሺኑጣ መጥቶ ሲባርካት ተመለከትሁ» ብሎ ነገራቸው። ወላጆቿ የመጀመሪያ ልጃቸው ባገኙት ሞገስና በቅዱሳኑ ቡራኬ እጅግ ተደሰቱ።

አንድ ቀን፥ ፋውዜያ ከ፰-፲፪ ወራት ዕድሜ ክልል ውስጥ ሆና፤ ቤተሰቡ በአል-ፌዚ ቤት ተሰብስበው ነበር። በቤቱ ሰገነት ላይ በተዘጋጀ ማረፊያ ቦታ ቁጭ ብለው ሳሉ፥ ፋውዜያ መሬት ላይ እየዳኸች ለመጫወት፤ ከእናቷ ዕቅፍ ካልወረድሁ ብላ አስቸገረች። እናት ደግሞ ልጇን ላለመልቀቅ ሲታገሉ፥ አያትዋ በመኻል ገብታ፥ ለምን አትለቂያትምና አትጫወትም? ስላለች፥ አውርዳ ለቀቀቻት። ሕፃኗ ግን ገና መሬት ከመንካቷ አምርራ አለቀሰች። ወዲያው ሰውነቷ ቀዝቅዞ ተዝለፍልፋ የሞተች መሰለች። እነርሱም ተደናግጠው ወዲያው ሐኪም ጠሩ።

በዚህ መኻል፥ እናቷ መሬት ላይ ጊንጥ በማየቷ፥ ልጇን እንደ ነከሰቻት ስላ ወቀች፥ «አባ ሺኑጣ! ድረስልኝ»[6] ብላ ጮኸች። ወዲያው አባ ሺኑጣ በላየር ሰፍፎ ታየ። ፋውዜያን ከእናቷ ተቀብሎ፥ ፊቷ ላይ እፍ ካለባት በኋላ፥ ግንባሯ ላይ በትእምርተ መስቀል አማተበ። ከዚያም ለጀኔፍየፍ «የእኛ ናትና ስጋት አይግባሽ!» ብሏት ተሰወረ። ፋውዜያም ወዲያው ነፍስ ዘራች። ያ ዕለትም እንደ ዳግም ልደቷ ተቁጠረ። ያም ሆኖ ግን፥ «የእኛ ናት» የሚለው ቃል እናትና አባቷን «አንድ ቀን ምን ትሆንብን ይሆን?» በሚል ስጋት ሁሌ ያሳቅቃቸው ነበር። ከዚህ ዕለት ጀምሮ ገዳም እስከገባችበት ጊዜ ድረስ፤ በየዓመቱ ሥዕለት እየያዙ ወደ አባ ሺኑጣ ገዳም ለምስጋና ይሄዱ ነበር። አባቷም እስከ ዕለተ ዕረፍቱ ድረስ (ከእርሷ ምንኩስና በኋላም) ይህን ማድረግ አላቋረጠም። ወደ ፊት እንደምናየው፤ አባ ሺኑጣ እናት ጌራኒን በገዳማዊ ሕይወቷም፥ ከብዙ ችግሮች ይታደጋት ነበር። ከፋውዜያ በኋላ አራት ሴቶችና ሁለት ወንዶች ልጆች ተወልደዋል። «ልጆቻቸው በጎልማስነታቸው እንደ አዲስ ተክል የሆኑ፥ ሴቶች ልጆቻቸውም እንደ አልፍኝ ያማሩና ያጌጡ» እንዲል (መዝ. ፻፵፫/፬፥፲፪)።

---

[6] አባ ሺኑጣ በሳዕላይ ግብፅ፥ በተለይ በመርዛም እንስሳት የተነደፉ ሰዎችን የማዳን ጸጋ (ሥልጣን) እንዳለው የታወቀ ነው። ማንም ሰው ቢሆን ጊንጥ ወይም ሌላ ተናዳፊ እንስሳትን ሲያይ፥ ወዲያው እርሱን መጥራት የተለመደ ነው። አባ ሺኑጣ ድረስልን/እርቅልን» ብለው ይጮኻሉ። ይደርስላቸዋል።

የወላዲተ አምላክ ምልጃ፦ የፋውዜያ ቤተሰብ ኑሮኣቸው የቅዱሳን በመሆኑ እግዚአብሔር ብዙ ተአምራትን አድርጎላቸዋል። በተለይ እናቷ ከእመቤታችን ጋር ባላት ጥልቅ ግንኙነት፤ ብዙ ጊዜ ትገለጥላታለች። ፋውዜያ ትንሽ ልጅ እያለች፤ የፈላ ውኃ እግሯ ላይ ፈሶባት ክፉኛ ተጎድታ ነበር። እግሯ ውኃ ቋጥሮ በጣም በመቍሰሉ ምክንያት፤ እናቷ ብዙ ዐይነት መድኃኒት ብትቀባትም ቍስሉ ሊድን አልቻለም፤ በለቅሶ እመቤታችንን እየተማጸነች ሳለች፤ ፋውዜያ ለስለስ ያለ አየር በእግሯ ላይ ሲነፍስና ሲዳብሳት ተሰማት። ወዲያው ቍስሏ ዳነ። ለምልክት ያህል እንኳን የቀረ ቍስል አልተገኘም።

የእናቷ በተአምር መፈወስ፦ እናቴ በኃይለኛ የሆድ ሕመም ትሰቃይ ነበር። የጌርጋ ሐኪም ምንም ሊረዷት አልቻሉም። ወደ ካይሮ ሄዳ ብትመረመርም፤ ውጤት አልባ ሆነ። እናቴ በዚህ ጊዜ የአራት ልጆች እናት የነበረች ሲሆን፥ በእያንዳንዳችን መካከል ያለው የዕድሜ ልዩነት የአንድ ዓመት ብቻ ነው። ቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም ቤተ ክርስቲያን አጠገብ ስለሆነ፥ ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚመላለሱትን ምእመናን፤ ሲሄዱና ሲመጡ እናያቸዋለን። በአንድ ሰንበተ ክርስቲያን፤ እናቴ በጸና በመታመሟ ምክንያት ስታቃስት እኔም አጠገቧ በረንዳው ላይ ቆሜ ነበር። ዐላፊ አግዳሚውን እያየች፤ እኔ እንደ ሰዉ ሁሉ አስቀድሼ ለመቍረብ አልታደልሁም፤ ብላ አምርራ አለቀሰች። የእርሷን ፅንባ ሳይ እኔም አብሬያት ማልቀስ ጀመርሁ። እርሷ እኔን ስታባብል፥ እኔም «እናቴ! እባክሽ አታልቅሺ እመቤታችን ትፈውስሻለች» አልኋት።

ዕለቱኑ ማታ፤ ወላዲተ አምላክ ሰማያዊ መንናጸፊያ ተንናጽፋና በደማቅ ክዋክብት ተከብባ መጥታ፥ እናቴን «ለምን ታለቅሻለሽ?» ብላ ስትጠይቃት፥ «ልጆቼ ገና ሕፃናት ናቸው። እመቤቴ! ከእኔ በኋላ ማን እንደሚያሳድጋቸው፥ ወይም በክርስቲያናዊ ሥነ ምግባርና በፈሪሐ እግዚአብሔር ታንፀው ማደግ እንደሚችሉ አላውቅም። እመቤቴ! ትልቋ ልጄ፥ አድጋ የወንድሞቿንና የእኅቶቿን ኀላፊነት መረከብ እስከምትችል ድረስ በሕይወት እቆይ ይሆን? ወይስ ከዚያ በፊት እሞታለሁ?» ስትላት፥ እመቤታችን አረጋግታ፥ «ነይ ከእኔ ጋር እንሂድ። ከኣንድ ጥሩ ሐኪም ጋር አገናኝሻለሁ» አለቻት። እናቴ በመጀመሪያ የኣባቴን ፈቃድ መጠየቅ አለብኝ ብላ መለሰች። እመቤታችንም፥ «ከጌታዬ እናት ጋር ልሄድ ነው ብትይው ይቃወምሻል?» ስትላት፥ እናቴ «ክብርና ምስጋና ለኣንቺና ለልጅሽ ይሁን፤ በፍጹም አይቃወመኝም» ስትል መለሰች።

እናቴና እመቤታችን ከቤት ወጥተው፤ ይጠብቃቸው የነበረው ሠረገላ ላይ ተሳፈሩ። ሠረገላው ይዟቸው መልካም መስክ ወዳለበት ሥፍራ ሄደ። እናቴ ወደ አንድ ትልቅ ሕንፃ ውስጥ ገባች። በሕንፃው ውስጥ መኝታ ያለው የተለየ ክፍል አለ። ሐኪሙም እዚያው ነበር። ወላዲተ አምላክ «ጊዮርጊስ! ና መርምራት» ስትለው ሐኪሙ «እመቤቴ! የእርሷ ነገር እንዳሰብሽለት ታውቂያለሽ!» አላት። እመቤታችንም «በኣማላጅነቴ በመማጸኗ፥ ለልጄ አሳስቤው አሁን እንደማትሞት (እንደምትቆይ) ቃል ገብቶልኛል። ታድያ ከነበሽታዋ ትመለስ ትላለህ?» አለቸው።

እናቴ አልጋው ላይ ተኛች። እመቤታችን ቅዱስ ጊዮርጊስን «እጅህን ሆዷ ላይ አድርግ» አለቸው። እርሱም «በመጀመሪያ በኣንቺ እጅ ይሁን ድንግል እመቤቴ!» አላት። እመቤታችን እጇን እናቴ የሚያማት ቦታ ላይ ስትጭን፥ ቅዱስ ጊዮርጊስም እንደ እርሷ አደረገ። ሆዷን ቀስ በቀስ ጫን ጫን አሏት። ከዚያም ከፍ ከፍ እያሉ ወደ ደረቷ አካባቢ ሲጫኗት፤ ከኣፏ ውስጥ የበለበሰ ሥጋ መሰል ነገር ወጣ። የወጣውን ነገር በጥጥ ጠቅልለው በእጇ አስያዟትና፥ «የቸግርሽ መንሥኤ ይህ ነበር» ብለው መልሰው ወደ ቤት አመጧት። እናቴ ከዕንቅልፏ እንደ ነቃች፥ ሁላችንንም ቀስ ቅሳ በሕልሟ የሆነውን ሁሉ ነገረችንና፥ በእጇ የያዘችውን የሥጋ ቁራጭ አሳየችን። አባቴም ወዲያው ለኣምላካችን ለእመቤታችንንና ለሰማዕቱ ውዳሴ Doxology & Theotokia[9] እናቅርብ (እንዘምር) አለን።

ጀኔፍየፍ በጥያቄዋ መሠረት ከበሽታዋ ተፈውሳ ረጅም ዕድሜ ኖረች። ተጨማሪ ልጆችም ወለደች። እንዲሁም እንደ ጸሎትዋ፤ ትልቋ ልጇ ፋውዜያ አድጋ ገዳም እስከምትገባ ድረስ በሕይወት ኖራለች። የጀኔፍየፍ ልጆች በሙሉ ስለ እናታቸው ቅድስና፤ ጽኑ እምነት፤ የማያቋርጥ ጸሎትና ከእግዚአብሔር ቅዱሳን ጋር ስላላት ወዳጅነት፤ በቃልም በግብርም ምስክሮች ናቸው።

ቤተሰባዊ ልግስና (ምጽዋት)፦ ለጋሥ የሆኑት የፋውዜያ ወላጆች፤ ምጽዋት የሚያደርጉት፥ ለተቸገሩት ገንዘብ በመስጠት ብቻ ሳይሆን፥ ምግብም አዘጋጅተው ይመግባሉ። ጀኔፍየፍ በየዕለቱ ለቤተሰቡ አባላት ምግብ ስታዘጋጅ፥ ነዳያኑንም ከግምት አስገብታ ነው። እንደ የነዳያኑ የቤተሰብ አባላት ብዛት እየመጠነች፤ ምግቡን ካዘጋጀች በኋላ፥ ከፋፍላ ታስቀምጥና፥ ፋውዜያ ከትምህርት ቤት ስትመለስ፤ በየመንደሩ ዞራ ታዳርሳለች። የጀኔፍየፍ ቤተሰብ በየዕለቱ ምግባቸውን ለመመገብ የሚቀርቡት፤ ቀዳሚ የሆነው የነዳያን ምገባ ካጠናቀቁ በኋላ ብቻ ነው።

አንድ ጊዜ፥ ከልጆቿ አንዷ «እናቴ! ገንዘብ እንሰጣቸው የለም እንዴ፥ ለምን ራስሽን በትርፍ ሥራ ታደክሚያለሽ?» አለቻት። ደጓ እናትም «ልጄ! እኛ በምንሰጣቸው ገንዘብ በጣም አስፈላጊ ነገሮችን ሊገዙ ይችሉ ይሆናል። ነገር ግን እንዲህ ያለ ምግብ አዘጋጅተው መመገብ አይችሉም» ብላ መለሰችላት። ጀኔፍየፍ ይህን ተግባር ስትፈጽም፥ ማንም እንዳያስተውላት ጥንቃቄ አድርጋ፤ ልጆቿን የምትልክበት ሰዓት፥ በጎዳናው ላይ ብዙም ሰው የማይታይበትን መርጣ ነው። ልጆቹ የተመረጠው ሰዓት ካልተስማማቸው፥ ፀሓይ ያቃጥለኛል ወይም ጨለማው ያስፈራኛል ብለው ሲያንገራግሩ «ትክክለኛና መልካም ሥራ እስከሠራችሁ ድረስ ጌታችን ከማንኛውም አደጋና ድካም ይታደጋችኋል» በማለት ታግባባቸዋለች።

[9] {Doxology፦ ለቅድስት ሥላሴ በዝማሬ የሚቀርብ ምስጋና።}

ለነዳያን ካላት መውደድና ኀዘኔታ ብዛት፤ የምታደርግላቸው እንክብካቤ በተለ
ያየ መንገድ ነው። ይህ ለጋስነቷ ደግሞ ቤቷን በበረከት የሞላ አድርጎላታል። በሁ
ለት በኩል መግቢያ ያለውን የጊቢዋን በር ያንኳኳ ችግረኛ፤ ቤት ያፈራውን ሳያገኝ
አይመለስም። በዕለተ ሰንበተ ክርስቲያን፤ ወደ ቤቷ ለመጡት ሁሉ ዳቦ ስታከፋፍል፥
ቆሞ ይመለከታት የነበረው ባሏ፤ ዱቄትና እርሾ ገዝተን ተጨማሪ ዳቦ መጋገር እን
ጀምር እንጂ፥ ይህ ነገር ሳያንሰን አይቀርም ሲላት፤ በልበ ሙሉነት «በሳምንቱ ከተ
መደበለት ቀን ውጪ ዳቦ አንጋግርም» አለችው። ይህ ቤቷን በበረከቱ በሞላላት አም
ላኳ ላይ ያላትን፥ ጽኑ እምነት ያሳያል።

ቤተሰቡ ከሊቀ መላእክት ቅዱስ ሚካኤል ጋር ያለውን የጠበቀ ግንኙነትም
መጥቀስ ተገቢ ነው። በሥዕል ቤታቸው ውስጥ ያለ የቅዱስ ሚካኤል ሥዕል ሥር፤
ሌት ከቀን ዕለት ዕለት የማይጠፋ መብራት አለ። በየወሩ በ፲፪ኛው ዕለት በዓሉን ያከ
ብራሉ። በዓመታዊ በዓሉ ዋዜማ ደግሞ፥ ማታ በሰሓን ዳቦና በጆግ ውኃ አድርገው
ከሥዕሉ ሥር ያስቀምጡታል። በማግሥቱ ጠዋት ሲነሡ፥ በዕለተ በዓሉ ሊቀ መላእ
ክት ቅዱስ ሚካኤል፤ ዳቦው ላይ በተአምር <u>ትእምርተ መስቀል</u> ሠርቶበት ያገኛሉ።
ጀኔፍየፍ ያንን ዳቦ ቆርሳ የዱቄት ዕቃ ውስጥ ትጨምራለች። ዱቄቱም ከዓመት
እስከ ዓመት ይበረክታል። በረከቱ ለዱቄቱ ብቻ ሳይሆን በጓዳው ውስጥ ላሉ የምግብ
ዐይነቶች በሙሉ ይተርፋል። ዳቦው ለቤተሰቡም ለነዳያኑም ያለ እጥረት የሚዳረስበ
ትና እርሷም የማትጨነቅበት እንዲሁም «ከተመደበለት ቀን ውጪ አይጋገርም»
የምትልበት ምሥጢርም ይኸው ነው።

የፋውዜያ አባትም በለጋስነቱ የታወቀ ሰው ነው። በኣቡ ሰይፊን ገዳም የሚያ
ገለግል አንድ ሀብታም ነጋዴ እንደ ነገረን፤ ለእርሱ ሀብትና ለንግዱ መስፋፋት
መሠረቱ የፋውዜያ አባት ነው። *ከኃጌ ሆኖ በማንኛውም እንቅስቃሴዬ ያበረታታኛል።*
አስፈላጊ የሆነውን ድጋፍ ሁሉ በማድረግ፥ በሁለት እግሬ እስክቆም ድረስ አልተለየ
ኝም። ይህን የሚያደርገውም ለእኔ ብቻ ሳይሆን ለማንኛውም ሰው ነው። እንዲሁም
ለሠራተኞቹም ሆነ፤ ለንግድ ሸሪኮቹ ስለ ክርስትና ሃይማኖት ይመሰክርላቸዋል። ከን
ግዱ ስኬት የተነሣ፥ አገልግሎቱ ብዙ አካባቢዎችን ይሸፍናል። እኔም ከሠራተኞቹ
አንዱ ነበርሁ።

በየወሩ አንድ ቀን የመምረጥ ልምድ ነበረው። የሚመረጠው ቀንም ከሌሎቹ
ቀናት የተሻለ ትርፍ የተገኘበትን ነው። የዕለቱን ገቢ (ትርፍ) ምንም ሳያስቀር ወስዶ
የጠረጴዛው መሳቢያ ውስጥ ያስቀምጠዋል። ከዚያም እጅግ ብዙ ቍጥር ያላቸው
ሠራተኞቹ፤ በዚያ በተመረጠ ዕለት፥ ወደ ቤታቸው ከመሄዳቸው በፊት ወደ ቢሮው
ይጠራሉ። ደጉ በለሃብት፥ እጁን በትንሹ ወደተከፈተው መሳቢያ ያስገባና፥ ለእያንዳ
ንዱ ሠራተኛ ገንዘብ ዘገን አድርጎ ይሰጣል። የሚሰጠውን የገንዘብ ልክ ስለማይቄ
ጠር፥ ሁሉም እግዚአብሔር እንደ ፈቀደለት ይደርሰዋል። ይህም ከወር ደሞዝ ውጪ

የሚደረግ ልገሳ ነው።

በዚህ የልግስና ሥራው ውስጥ፤ እጅግ የሚያስደንቀው ደግሞ፥ ለእያንዳንዱ
ሰው የሚደርሰው የገንዘብ መጠን እኩል ባይሆንም፥ ሳይበዛ ሳያንሱ፥ ጉድለታቸውን
በትክክል የሚሞላ መሆኑ ነው። በረከተ እግዚአብሔር ያደረበት ገንዘብ ነውና፥ በኣ
ንድ ምክንያት ተጨማሪ ገንዘብ አስፈልጎት ሲጨነቅ የነበረ ሠራተኛ፤ በዚህ መንገድ
የሚሰጠው ገንዘብ፥ ለሚፈልገው ጉዳይ በቂ የሆነና የማይተርፍ የማያንስ ሲሆን፥
ብዙ ችግር የሌለበት ደግሞ መጠነኛ ብር ይደርሰዋል።

<u>ሰሐመማንና ስመበስታት የሚሰጥ ስገልግሎት</u>፦ ጀኔፍየፍ ልጆቿ የኣገልግሎት ፍቅር እን
ዲያድርባቸው ጥሩ መሠረት ጥላላቸዋለች። ለምሳሌ አንዲት ከወንድሟና ከሚስቱ
ጋር የምትኖር፤ አካሏ ሽባ የሆነ ጎረቤት ነበረቻት። ይህች ሴት ወንድሟና ሚስቱ
ለኣንዳንድ ጉዳይ ወደ ሌላ ሀገር ሲሄዱ፥ ባዶ ቤት ውስጥ ብቻዋን ለመቀመጥ ትገደ
ዳለች። በዚህ ጊዜ ጀኔፍየፍ ልጆቿ እንዲመግቧት፤ ቤት እንዲያጸዱላትና የምትፈል
ገውን ሁሉ እንዲያደርጉላት ትልካቸዋለች። ወላጆቻቸው ወይም ባላቸው የሞቱባቸ
ውንም እንዲሁ፥ ምግባቸውን እየላከች ትንከባበባቸዋለች። ልጆቹ ምግቡን አድርሰው
ብቻ አይመለሱም፤ ቤት እንዲያጸዱና አስፈላጊውን ሁሉ እንዲያደርጉ ታሳስባቸዋለች።
እንዲሁም የልጆቹን የኣካል መጠን (ልክ) ለክተው ያመጡላትና ልብስ ሰፍታ ትልካለች።
እርሷ ራሷም እየሄደች ከእነርሱ ጋር ትጸልያለች፤ መጽሐፍ ቅዱስ ታነብላቸዋለች።

ፋውዜያ በዚህ የተባረከ ቤተሰብ እጅ በማደጓና፥ የእግዚአብሔርን በረከት እያ
የች በመኖሯ፥ ትንሿ ልቧ ውስጥ ያደረባትን የጠለቀ መንፈሳዊነት የሚያውቀው፤
ይህን ጸጋ ያሳደረባት አንድ እግዚአብሔር ብቻ ነው። ከሩኅሩኀና የውኃ ምንጭ እየ
ጠጣች፤ የወላጆቿን የጽኑ እምነት ጥሪት እየሰበሰበች፤ ማንም ለመረዳት በማይች
ለው የቅድስና መስመር አደገች። በወንጌል «ማርያም ግን ይህን ነገር ሁሉ በልቧ እያሰበች
ትጠብቀው ነበር» እንዲል፤ ፈጣሪዋን እንዴት ማስደሰት እንዳለባት ብቻ የምታስብ
ታማኝ ልጅ ሆነች (ሉቃ.፪፥፲፱)።

የፋውዜያ ሁለተኛ እኅት የሆነችው ወ.ሮ ፋይቃ ያሳ፤ ስለ ውድ እኅቷ
ጣማፍ ኄራኒ የቅድስና ሕይወት እንዲህ ብላ መስክራለች፦ ፋውዜያ ገና ከልጅነቷ፥
ፈጣሪዋን በሙሉ ልብ የምትወድና ለወላጆቿም ታማኝና ታዛዥ ነበረች። ጸሎት፤
ጾም፤ ንስሐ፤ ማስቀደስና መቍረብ እንዲሁም የሰንበት ትምህርት ቤት ጉባኤያትን
መከታተል፥ በፍጹም የማይታጎል መሠረታዊ ሥራዋ ነው። ለኦርቶዶክሳዊት ሃይማ
ኖቷ ፍቅር ያላትና የቅብጥን ቤተ ክርስቲያን ክብር አስጠባቂ ነበረች።

አንድ ጊዜ ትዝ ይለኛል፥ የጌርጋ ጠቅላላ ሆስፒታል ነርስ የሆነ ባል ያላት
ኣንዲት ሴት ነበረች። ምንም እንኳን፥ ቤተሰቦቿ የኦርቶዶክስ ሃይማኖት ተከታይ

ቢሆኑም፤ እርሷ ግን «የነፍስ ድኅነት - (The Salvation of the Souls)» የተሰኘ እምነት ድርጅት አባል ናት። በቤቷ በምታካሂዳቸው ጉባኤያት ምክንያት፤ በኣካባቢዋ የሚኖሩና ምንም የማያውቁትን ሰዎች ትኰረት፤ ወደ ተሳሳተ እምነት መሳብ ጀመረች። ከዚህም አልፋ፥ ወደ ጌርጋ አጥቢያ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ሄዳ፤ ካህናቱን በገንዘብ በመደለል፥ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በየሳምንቱ ጉባኤ አዘጋጅታ፤ የኑፋቄ ትምህርቷን ማስተላለፍ ጀመረች። ብዙ የእግዚአብሔር ቃል የጠማቸው ክርስቲያኖች፥ እንዳለመታደል ሆኖ በእጇ ወደቁ።

ከዕለታት አንድ ቀን፥ እኅቴ ፋውዚያ፤ በዚህ የኣካባቢውን ክርስቲያን ባጥለቀለቀውና ባሰጠመው ጉባኤ ላይ እንድትገኝ ጥሪ ደረሳት። ሄዳ ጉባኤውን ተካፈለች። በመጨረሻ ላይ፥ ያቺ ሴት «<u>የዳናችሁ እጃችሁን አውጡ</u>» ስትል በመስማቷ፤ እኅቴ በጣም አዘነች። ከዚህ በኋላ የዚህ ጉባኤ ተካፋይ የሆኑትን ወጣቶች ቀርባ ጓደኛ በማድረግ ወደ ቤታችን እንዲመጡ ጋበዘቻቸው። እቤት ሲመጡ፥ ሰለ ትክክለኛዋና እውነተኛዋ ሃይማኖት አስተምራ፤ በሴትየዋ የተሳሳተ ትምህርት ከመጠለፍ እንዲድኑ በኣጽንኦት አሳሰበቻቸው። ስለ ነገረ ድኅነትና ምሥጢረ ንስሐ፥ ከኣባ መቃርስ አስተምህሮ ጋር እያጣቀሰች አብራርታ ነገረቻቸው። አባ መቃርስ እስከ ሕይወቱ ፍጻሜ ድረስ፤ እነዴት በሰይጣን እንደተፈተነና በግልጽ እየመጣ <u>መቃርስ! አንተኮ ድነሃል</u> ይለው እንደ ነበረ፤ ታላቁ አባት ግን <u>አይ! ገና ነኝ፣ ገና አልዳንሁም</u> ብሎ እንደሚመልስለትና፥ በመጨረሻ ግን፤ ነፍሱ ወደ ሰማያት ስታርግ <u>አዎ! አሁን ድኖለሁ!</u> እንዳለ ተረከችላቸው።

በእምነቷ ጽናት ምክንያት፥ ጸጋ እግዚአብሔር አልተለያትምና፤ ብዙዎችን ከጥፋት ውኃ (ከኑፋቄ) መለሰቻቸው። ወደ እርሷ ትምህርት የሚመጡት፤ ብዛታቸው በጨመረ ቍጥር፤ የዚያኛው ጉባኤ ተካፋዮች፥ ቍጥር ከዕለት ዕለት መመናመን ጀመረ። መናፍቋ ሴት፥ ይህ የቍጥር መመናመን የመጣው በፋውዚያ ምክንያት መሆኑንና፤ ፋውዚያም ለምንኵስና እየተዘጋጀች መሆኗን ስትሰማ፤ እንደ ሞኝ ቄጥራት፥ የሰው ሁሉ መሳለቂያ ልታደርጋት ፈለገች። በሚቀጥለው ጉባኤ ላይ፥ መናፍቋ ለባኪት፤ በገዛ ቤቱ ውስጥ እየሰበከች (ክብር ምስጋና ለእርሱ ይሁንና)፤ ቅዱስ ጊዮርጊስ እንደ ማንኛውም ተራ ሰው መሆኑን በንዴት ተናገረች። የመላእክት ሕይወት የሆነውን የምንኵስና ሕይወትም ሆነ ሰማዕትነት፤ የማያስፈልግ ነው፤ ቅዱሳን የሚባል ነገር የለም። በማለት በድፍረት ተናገረች። ወጣቷ ፋውዚያም፥ ተነሥታ ለእያንዳንዱ የክሕደትና የስድብ ቃል፥ ቀና የሆነ መጽሓፍ ቅዱሳዊ መልስ ትሰጣት ጀመረች።

በዚህ ጊዜ ሴትየዋ ራሷን መቆጣጠር አቅቷት ተዘለፍልፋ ወደቀች። ፋውዚያም በጉባኤው ለተገኙት፥ አያችሁ! ርኵስ መንፈስ አድሮባታል።[10] ታድያ በርኵስ መንፈስ ልንመራ ወይም ቃለ እግዚአብሔርን ልንሰበክ ይገባናል እንዴ? ብላ ጠየቀች

[10] {በእኛ ቤተ ክርስቲያን፥ ርኵሳን መናፍስት ሲጋለጡ፤ ያደሩበትን ሰው እንደሚጥሉትና እንደሚያንዘፈዝፉት።}

ቸው። በዕለቱ አብሯቸው የነበረው የሰንበት ትምህርት ቤቱ ኀላፊ፤ እቤቷ ድረስ ሄዶ ለፋ ውዚያ አከብሮቱን ገልጦላታል። የቤተ ክርስቲያኒቱ አገልጋይ የሆነው ቄስ ግን፥ በዘመኑ ጣዖት በ«ገንዘብ» ተደልሏልና አወገዛት። ይህን ያዩ፥ አብረዋት የነበሩ ወጣቶች፥ ፍቅረ እግዚአብሔር በውስጣቸው በመቀጣጠሉ፤ አይዞሽ እያሉ አረጋጓት። እርሷም «አባቴ! ከዚህ በኋላ ይህች ሴት ወደዚህ ቅዱስ ሥፍራ ብትገባ፥ ቅዱስ ጊዮርጊስ ያዝንብሞታል» አለችው። ከዚያም ለእግዚአብሔር ቤት ቀናኢ ወደ ሆኑ፥ አባ ሐና ሰላማ የተባለ ቄስ ዘንድ ሄዳ ስታማክረው፤ መጨነቅ እንደሌለባትና ለተከሰተው ችግር ሁሉ እርሱ ኀላፊነቱን እንደሚወስድ ነገራት።

የዚያኑ ዕለት ሌሊት ላይ፤ ቤተ ክርስቲያኑ በታላቅ ብርሃን ሞላ። የኣካባቢው ነዋሪዎች ሁሉ፤ ብርሃኑን ያዩና ድምፅም ይሰሙ ነበር። ወደ ቤተ መቅደስ ሲገቡ ሰማዕቱ ቅዱስ ጊዮርጊስን አዩት። እርሱም «ይህች ሴት ከእንግዲህ ወደዚህ ቤተ ክርስቲያን እንዳትገባ!» ብሎ ተናገረ። ይህ ተኣምር ከተፈጸመ በኋላ፥ አባ ሐና ሰላማ ለፋውዚያ ያለው አክብሮትና ፍቅር ጨመረ። ተጨማሪ ቅዱሳት መጻሕፍትንም እየሰጠ እንድታነብና ይበልጥ እንድትጠነክር ይመክራት ነበር። ከሰጣት መጻሕፍት ውስጥ፥ በቅዱስ ያዕቆብ ኣል-ሳሩጂ (St.Ya'qub al-Saruji) ወይም (acob of Saruj) (፬፻፶፪-፭፻፬ ዓ.ም.) የተደረሰ የቅዱሳንና ሰማዕታት ገድልና ውዳሴ ይገኝበታል። እንዲሁም ስቅዳሴ እንዳትቀር አዘውትሮ ያሳስባታል።

አባ ጊዮርጊስ የተባለ፤ የሊቀ መላእክት ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን አገልጋይም፥ ብዙ ጊዜ ወደ ቤታችን ይመጣ ነበር። ይህ ካህን መመንኰስ እንደማይገባትና፤ ከመነኰሰችም እንደሚያወግዛት ተናገራት። ፋውዚያ በሰማችው ማስጠንቀቂያ አዝና አምርራ አለቀሰች። አባ ሐና ሰላማም ይህን ሲሰማ፥ እርሷን ለማረጋጋት ልዩ ጉባኤ አዘጋጅቶ ጠራትና «ሁሉንም ለእግዚአብሔር እንድትተው፤ እግዚአብሔርም የሚበጃትን እንደሚያደርግላት» መከራት። አወግዝሻለሁ ያላት አባ ጊዮርጊስ፤ በዚያው ሰዓት መጥቶ ሐሳቡን መቀየሩንና መመንኰስ እንደምትችል ነገራት። እንዲሁም በሥርዓተ ምንኵስናዋ ላይ ጸሎት ካደረጉላት ካህናት አንዱ እርሱ ነበር።

ፋውዚያ ጸጋ እግዚአብሔር ያደረባት ገና ከልጅነቷ ነው። «ነገር ግን በእናቴ ማሕፀን ሳለሁ የለየኝ በጸጋውም የጠራኝ እግዚአብሔር . . .» እንዲል፤ ከቤተሰቡ ሁሉ መርጦ ብቻም አልተዋትም። ወርቅ በእሳት ይፈተናል እንዲሉ፥ ሕይወቷን ሁሉ እንደ ነጠረ ወርቅና እንደ ውድ ዕንቊ አከበራት እንጂ (ገላ.፩፥፲፭)። በጸመ ፍልሰታ እኽል የምትቀምሰው፥ በቀን አንድ ጊዜ ሲሆን፤ እሱንም በጣም አምሽታ ዳቦ በጨው ብቻ ነው። ከዚህ ውጪ ምንም አትቀምስም። አንድ ቀን እናቴ ፍራፍሬ ቆርጣ እንድትበላ ስትሰጣት፥ «መጥፎ ሽታ አለው፤ ምናልባት ሳይበሰብስ አይቀርም» ብላ መለሰችላት።

እንዲሁም ወደ ቤተ ክርስቲያን ካልሄደች በስተቀር፥ ሱባኤዋን የምታሳልፈው

ነበራት። በኣስፈላጊው ሰዓት ከተጠቀመችበት በኋላ ወዲያው ኣውልቃ ቦታው ትመልሰዋለች። ኣንድ ቀን ግን ሥራ በዝቶባት ስለ ነበረ፤ ጊዜ ኣግኝታ ቦታው እስክትመልሰው ድረስ፤ ኣውልቃ ኣጠገቧ የነበረ የትራስ ልብስ ላይ ኣኖረችው። የጽዳት ሠራተኛዋ ስትመጣ፥ የሚታጠበውን ልብስ ጠቅልላ፤ የቤቱ የላይኛው ክፍል በረንዳ ላይ ስታሰ ቀምጥ፥ ወርቁ ሾልኮ ወደቀ። መውደቁን ያየ ሰው ግን ኣልነበረም። ኣናቴም ጉዳይዋን ጨርሳ፥ ወርቋን ወደ ቦታው ለመመለስ ስትፈልግ ኣጣችው። ከሠራተኞቿ ኣንዳቸው እንደወሰዱት በማሰብ፤ እንዲመልሱላት ያደርግ ዘንድ፥ ወደ ቅዱስ ጊዮርጊስ ጸለየች።

ኣባቴ ከሥራ ሲመለስ፤ ምንም እንኳን እናቴ ንዴቷን ላለማሳየት ብትሞክርም፤ ከሁኔታዋ ተረድቶ ምን እንደ ሆነች ጠየቃት። ውድ የሆነ የኣንገት ወርቋ እንደጠፋባት ስትነግረው፥ ቀለል በማድረግ ብዙም እንዳታዝን ኣሳሰባት። እርሷም በሙሉ መተማመን፤ ቅዱስ ጊዮርጊስ ያመጣዋል! ስትለው፥ «ቅዱስ ጊዮርጊስ ለእንደዚህ ያለ ተራ ነገር ጊዜ ይኖረዋል? ይልቁንም ወርቁን ያገኘው ሰው፤ ምናልባት እግዚኣብሔር ለችግሩ ሊደርስለት የፈለገው ይሆናል» ኣላት። በዚህ ንግግር ላይ ኣያሉ፤ ቤቱን ጥዑም መዓዛ ያለው የዕጣን ሽታ ኣወደው። ወዲያው ቅዱስ ጊዮርጊስ የወርቁን ሐብል ወደ ሁለቱ ሲወረውርላቸው ተመለከቱ።

<u>የፈዩሙ ሊቀ ጳጳስ ኣንባ ኣብርሃም (መፍቀሬ ነዳያን)</u>፦ መፍቀሬ ነዳያን የሆነው፥ የፈዩሙ ሊቀ ጳጳስ ኣንባ ኣብርሃም[11]፤ ከቤተሰቧ ጋር ያለው ልዩ ቅርበት፥ በቤታችን ውስጥ ጠረጴዛ ላይ የምናስቀምጠው፥ የኣባ ኣብርሃም ትልቅ ቅዱስ ሥዕል ኣለ። ብዙ ጎረቤቶቻችንና እናቴን ቤተ ክርስቲያን የሚያውቋት የቤት እመቤቶች፥ በየቤቱ እየሄዱ የመጠያየቅ ልምድ ኣላቸው። በዚህ የጉብኝት ጊዜኣቸው በሚያደርጉት ውይይት፥ እናቴ ከማንኛውም ዐይነት የሐሜት ወሬ ራሷን ለማራቅ ትሞክራለች። የምንኖርባት ከተማ ኣነስተኛ በመሆኗ፥ ኣብዛኛዎቹ ነዋሪዎቿ ይተዋወቃሉ። በኣንድ ዕለት እንደ ተለመደው፤ እኛ ቤት ተሰብስበው ሳሉ፥ ኣንዷ ወይዘሮ፤ ስለ ኣንድ ቤተሰብ መናገር ጀመረች፤ ሌሎቹም ቀጠሉ። ስለ ሰው የምትጨነቀው እናቴ ግን፤ ስሜታቸውን በማይጎዳ ሁኔታ፥ እንዴት ልታስቆማቸው እንደምትችል ማሰብ ጀመረች። ከኣንዴም ሁለቴ፤ በተዘዋዋሪ መንገድ ከሐሜቱ ልትገታቸው ብትፈልግም፥ ኣልተረዷትምና ሳይሆንላት ቀረ።

ከዚያ ጠረጴዛ ላይ ወደ ነበረው የኣባ ኣብርሃም ሥዕል ተመልከታ፤ እንዲረዳት በልቧ ተማጸነች። ወዲያው ሥዕሉ ያረፈበት ጠረጴዛ፥ ሦስት ጊዜ ሲንኳኳ ሁሉም ሰምተው ደነገጡ። ዙሪያቸውን ቢያማትሩ ሌላ ሰው የለም። ተረጋግተው ወደ ሐሜታቸው ሲመለሱ ጠረጴዛው በድጋሚ ተንኳኳ። ኣሁን ግን ሥዕሉ ተንቀሳቅሶ የኣባ ኣብርሃም እጅ ከፍሬሙ ኣልፎ ሲወጣ ተመለከቱ። ድርጊታቸው ትክክል ኣለመሆኑን ለመግለጽ ጠረጴዛውን በጣም መታው። ጉዳዩ ግልጽ ስላልሆነላቸው

[11] {የኣንባ ኣብርሃም መፍቀሬ ነዳያን ታሪክ፤ ዝክረ ቅዱሳን ዘተዋሕዶ ፭ኛ መጽ./ ኣዜብ በርሄ/ ኣዲስ ኣበባ (በ፳፻ ዓ.ም. ኣትም ገጽ ፻፵-፻፷፫፣ በ፳፻፬ ዓ.ም. ኣትም ገጽ ፻፶፪-፻፶፬)፤ ላይ ይገኛል።}

በክፍሏ ሆና ከማንም ሳትተያይ ነው። ብዙ ጊዜዋን ጌርጋ በሚገኘው የቅ.ማ.ቤ.ክ. ክንደኖቿ ጋር ታሳልፋለች። በተለይ በኣጽዋማት ጊዜ በየዕለቱ እየተገናኙ በተመሰጠ በመጸለይና በዝማሬ ጊዜኣቸውን ያሳልፋሉ። ከዚያም ቤተ ክርስቲያኑን ኣጽድተው ወደ ቤታቸው ይመለሳሉ። በተለይ ቤተ ክርስቲያኑን በማጽዳት ሥራ ቋሚዎቹ እነርሱ ነበሩ። ይህን ኣገልግሎት በይበልጥ እንዲገፋበት የሆነው፥ ገና ማጽዳት በጀመሩበት ዕለት ባገኙት ታላቅ በረከት ነው።

ቤተ ክርስቲያን የማጽዳቱን ሐሳብ ያቀረበችው እኅቴ ነበረች። የሐሳቧ መንሥኤም፥ ለዚህ ተግባር የተሠማራው ቁስ ደካማ ሽማግሌ በመሆኑና የሚረዳው ሰው ስለሌለ ነው። ቤተ ክርስቲያኑ ኣቧራ ከመልበሱም ሌላ፤ የሸረሪት ድር በየቦታው ይታይ ነበር። በዚያ በመጀመሪያው የጽዳት ቀን፥ እርሷና ጓደኞቿ ያንን ሁሉ ቆሻሻ በማጽዳት ሲደክሙ ነበር የዋሉት። ልክ ሥራቸውን ጨርሰው ሊወጡ ሲሉ፥ እመቤታችን ተገልጣላቸው «በስሜ የተሰየመውን፥ የልጆችና የጌታዬን ቤት እንዲህ ኣድርጋችሁ በማጽዳታችሁ ደስ ኣሰኝታችሁኛል» ብላ ባርካቸው ተሰወረች። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ፥ የጽዳቱ ሥራ በየሳምንቱ ቀጠለ። የሚሠሩትም በፍጹም ትጋትና በፍቅር ነበር። ኣንዳንድ ጊዜ እኖን ታናናሽ እኅቶቿንም ይዛን ትሄድና፥ በጸሎቱና በጽዳቱ ታሳትፈናለች። ለሁላችንም የሥራ ኀላፊነት ትሰጠን ነበር። በምታደርገው የሥራ ክፍፍል የኣስተዳደር ችሎታዋን ተገንዝቤበታለሁ። ይህም ከብዙ ጸጋዎቿ ኣንዱ ነው።

ሌላው ጸጋዋ ደግሞ ገና በወጣት ዕድሜዋ፤ ከኣረጋውያኑ በበለጠ ሁኔታ፥ በጎ ግግሯ ሰውን የማሳመን ችሎታዋ ወይም ኣንደበተ ርቱእነቷ ነው። ለምሳሌ ልጂ የሞተባት ጎረቤታችንን፥ ማንም ሊያጽናናት ባልቻለበት ሰዓት፤ ፈውዜያ በየዕለቱ ወደ ቤቷ ተመላልሳ፤ ከመጽሐፍ ቅዱስ ቃል እያጣቀሰች በመምከር፥ ፍጹም ኣረጋግታታለች። ሀብተ ትንቢትም ተሰጥቷታል። ይህን ጸጋ የሰጣትን ፈጣሪዋን በደስታ ታመሰግናለች።

ኣንድ ቀን ቤተ ክርስቲያን እያጸዳን ሳለን፤ ቶሎ ቶሎ በሉና ወደ ቤት እንሂድ። ኣረጋዊቷ ጎረቤታችን የልጂን ልጅ ልካ ታስጠራናለች ኣለችን። ይህን ካለች ከግማሽ ሰዓት በኋላ ወደ ቤት እንደተመለስን በራችን ተንኳኳ። ስንወጣም እንዳለችው መልእክተኛዋ ልጅ ፈውዜያን፤ ኣያቴ «ስለምፈልግሽ እባክሽ ቶሎ ኑይ» ብላሽ ለች ኣለቻት። ሁላችንም ተደንቀን እንዴት ቀድመሽ ኣወቅሽ ስንላት፥ ትሕትና በተሞላ ኣንጋገር «ሰይጣን ነው ይህን ያደረገው። ምክንያቱም ለቀጣይ ዱላው እመቻችለት ዘንድ፤ ራሴን ከፍ ከፍ እንዳደርግና በትዕቢት እንድጠመድ ሲዘይድ ነው» ኣለችን።

<u>ታላቁ ሰማዕት ቅዱስ ጊዮርጊስ (ዘዕዱ)</u>፦ እናት ኄራኒ፥ ቤተሰቧ ከሊቀ ሰማዕታት ቅዱስ ጊዮርጊስ ጋር ያለውን ወዳጅነት ስትናገር፦ እናቴ ከሰማዕቱ ጋር ያላት ወዳጅነት እጅግ ልዩ ነው። በበዓላት ቀን ብቻ የምትጠቀምበት፤ ኣንድ ትልቅ የኣንገት ሐብል

ግራ ተጋቡ። እናቴም «እንደ እውነቱ ከሆኑ ሰው እያማን ነበር። ይህም ፍጹም አግ
ባብ አይደለም። ሰዎችን ልናማቸው ሳይሆን ልንጸልይላቸው ይገባናል» አለቻቸው።

<u>አቡ ሐልቃ</u>ኑ የጸሎትና ምጽዋት ሕይወትና፤ ለቅዱሳኑ ያላቸው የላቀ ፍቅር የእነ ፋው
ዜያ ቤት ጸጋ ብቻ ሳይሆን፤ የዘመዶቻቸውም ጭምር ነው። እርሷም የእናቷ አባት
ስለ ሆኑት አያቷ፤ «ቃዋጋ ማታ አል-ፊዚ» ብዙ ጊዜ ትነግረናለችኑ አያቴ በጣም
የጸሎት ሰው ነበር። በየዕለቱ ማታ ማታ፤ ቤተሰቡን ሁሉ ሰብስቦ የምሽትና የሌሊት
ጸሎቱን ያደርሳል። ውዳሴ ማርያም ካነበበልን በኋላ፥ ከመጽሓፍ ቅዱስ የተወሰኑ
ጥቅሶች አንብቦ ያብራራልናል። ከዚያ ደግሞ ጥቂት ገድላት ወይም ተኣምራት ይነግ
ረንና ወደየመኝታችን እንሄዳለን።

እንደ ሊቀ ዲያቆንነቱ፥ በቅዳሴ ያገለግላል። በሰባ ዓመት ዕድሜው መቋሚያ
ውን ተደግፎ ቆሞ ረጅም ጸሎት ያደርሳል። ቤተ ክርስቲያን ካገለገለ በኋላ ደግሞ፤
በቅጽረ ቤተ ክርስቲያኑ በሚገኝ አግዳሚ ወንበር ላይ፥ ጋደም ብሎ የማረፍ ልምድ
ነበረው። በአንድ ጀርባው ላይ ጉትቻ ያደረገ ወጣት ልጅ በተደጋጋሚ፥ ይገለጥለት የነ
በረ ሲሆን፥ ይህ ወጣት ለሁለት ዓመታት የኣያቴን ልብስ እየጎተተ «አያቴ! ተነሥና
ጸልይ፤ ለጸሎት ተነሥ እንጂ!» ይለው ነበር። አንድ ቀን፥ አያቴ ደክሞት ዐረፍ እነ
ዳለ፥ ወጣቱ መጥቶ በተለመደው ሁኔታ ተነሥ አለው። አያቴም ይህ የማን ልጅ እነ
ደሆነ ማወቅ አለብኝ! ብሎ ወሰነና ሊይዘው ተነሣ። ልጁ ግን እየሮጠ ወደ መቅደስ
ገባ። አያቴም ተከትሎት ገባ። ልጁ ከመንበሩ ጀርባ ስለተሰወረበት እስኪወጣ ጠበ
ቀው። ብዙ ከጠበቀው በኋላ፥ እንደማይወጣ ሲረዳ፤ አንድን ካህን ይህ በአንድ ጀርው
ላይ ሎቲ ያደረገ ልጅ ማን እንደ ሆነ ጠየቀው። ቄሱም <u>አቡ ሐልቃ</u>[12] ሊሆን ይችላል
ብሎ መለሰለት»።

አያቴም በድንጋጤ ቁጭ ብሎ አለቀሰ። «የጌታዬ ሰማዕት! እባክህ ይቅር በለኝ»
እያለ፥ ለሦስት ቀናት በጸምና በጸሎት ቆየ። በኣራተኛው ቀን፤ ሕፃኑ ሰማዕት ቅዱስ
ቂርቆስ ተገልጦ እንዳስለመደው «አያቴ! ተነሥ ጸልይ» አለው። አያቴም «የጌታዬ ሰማ
ዕት እባክህ ይቅር በለኝ!? አንተን በማሯሯጥ ስሕተት ፈጽሜኣለሁና» አለው። ሕፃኑ
ቅዱስ ቂርቆስም «ይቅር ብዬሃለሁ አያቴ!» አለው። ከዚህ በኋላ እስከ አያቴ ዕለተ
ዕረፍት ድረስ፥ እንዳስለመደው እየመጣ ለጸሎት ያስነሣው ነበር። ወዳጅነቱን ከሕፃኑ
ቅዱስ ቂርቆስ ጋር ያጠነከረው አያቴ፤ «ለታመሙ ወገኖቼ ሁሉ ፈውስን ለምንላ
ቸው» እያለ ይጠይቀው ነበር። ሕፃኑ ቅዱስ ቂርቆስም እንዲህ በተጠየቀ በማግስቱ
«ፈውስ የጠየቅህለት ሰው ተሻለው? ወይስ ከዚች ምድር በሞት ተለየ?» ብሎ ይጠይ

[12] {ቅብጦች ሕፃኑ ሰማዕት ቅዱስ ቂርቆስን፥ «አቡ ሐልቃ» (Abu Halqa) ብለው ይጠሩታል። ትርጉሙም የጀር
ገጥ የሚያደርግ (ያለው) ማለት ነው። ቅዱስ መርቆሬዎስን ሁለት ሰይፍ ያለው ሰማዕት ፥"አቡ ሰይፉ"
እንደሚሉት።}

ቀዋል። ሰውየው አርፎ ከሆነም፤ «ይህ ፈቃደ እግዚአብሔር ነው» ብሎ ያጽናናዋል።

በልጅነቴ፥ ከኣያቴ ጋር ሆኜ፤ የሚያደርገውን ሁሉ እመለከትና እከታተል ነበር። መልካም ግብሩም እስካሁን ውስጤ ታትሞ ቀርቷል። የራሱ የሆነ ቦታ ያለው፤ ለሕንፃ መሣሪያ የሚውል እንጨት ነጋዴ ነበር። ልጆች ሆነን ከእኅቶቼና ወንድሞቼ ጋር ወደ ሥራ ቦታው እንሄዳለን። ሲመሽ «አም ሙሳ»[13] የተባለውን የታክሲ አሽከርካሪ ጠርቶ ወደ ቤት ውሰዳቸው ይለዋል። እኔ ግን አብሬህ እቆያለሁ ብዬ ስለማስቸግር፤ ይፈቅ ድልኝና ከእርሱ ጋር አምሽቼ አብረን ወደ ቤት እንሄዳለን።

አብሬው ሳመሽ፥ የሚሠራውን ነገር ሁሉ ስለምከታተለው፤ ያየሁትን ለማ ንም እንዳልነ ግር ቃል አስገብቶኛል። «አያትሽ የት ቆይተሽ መጣሽ ብትልሽ ምን መልስ ትሰጫታለሽ?» ሲለኝ «እኔ እንጃ እላታለሁ» ብዬ እመልስለታለሁ። እርሱም «ይሄማ ዋሸሽ ማለት ነው። የምታውቂውን ነገር እንዴት እኔ እንጃ ትያለሽ? ስለዚህ ከኣያትሽ ጋር የት ቆይታችሁ መጣችሁ? ስትልሽ፤ እርሱን ጠይቂው በያት» አለኝ።

በምሽት ቆይታችን በሄደበት ሁሉ፤ አብሬው ልሄድ ታክሲው ውስጥ ስገባ፥ መኪ
ናዎ በገንዘብ የተሞሉ ፖስታዎችና የተለያዩ ፍራፍሬዎች ተጭና አገኛታለሁ። ተፈላጊው
ቦታ ስንደርስ፤ ከመኪናው ወርዶ በየቤቱ እየሄደ፥ ያዘጋጀውን ዕቃ በሩ አጠገብ ያስቀ
ምጥና በራቸውን ያንኳኳል። በሩ እየተከፈተ መሆኑን ሲረዳ፤ ወጥተው ሳያዩት በፍ
ጥነት ከሥፍራው ዞር ይላል። እኔም ከሥሩ እየተከተልሁ እርሱ የሚያደርገውን አደ
ርጋለሁ። የያዘውን ስጦታ፥ በዚህ ሁኔታ በየነዳያኑ ቤት አዳርሶ ሲጨርስ ወደ ቤት
እንመለሳለን። አያቴ የት ቆይተህ መጣህ ስትለው፥ «አንድ ጉዳይ ነበረኝ» ይላታል።

<u>የፋወዚያ ሰምንኩስና አነሣስ</u>ኑ በሲራክ ፵፯፥፪ «ስቡን ከድኅነቱ መሥዋዕት እንደሚለዩ እንደዚሁ
ዳዊት ከእስራ ኤል ልጆች ተለየ» እንዲል፥ ፋውዜያም እንዲሁ ነበረች። ይህ ጥቅስ በእርሷ
ሕይወት ተፈጽሟል የሚያሰኘውም፤ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ኄራኒን የገዳሙ እመ
ምኔት እስክትሆን ድረስ ምርጫው መሆኗን፥ በብዙ መንገዶች መግለጡ ነው። በዚህም
በሰማያት ታላቅ ደስታ ሆነ። ገና ከልጅነቷ ነገረ ሃይማኖትን አጣጥማ ያደገችው ፋው
ዜያ፤ ወደ ሙሉ መንፈሳዊ ሕይወት ካልገባች ደስታ እንደማታገኝ ይሰማት ነበር። የእ
ርሷ ልምድም ሆነ ምኞት፤ ጸሎትና ውዳሴ ማድረስ፤ ቅዱሳት መጻሕፍትን ማንበ
ብና ለገድል መዘጋጀት ነው። ከእኅቶቿ ጋር መጫወት አያስደስታትም። ያኔ የእርሷ
ፍላጎትም ሆነ የደስታዋ ምንጭ፤ ጊዜዋን ከእናቷ ሥር ሥር እያለች ማሳለፍና፤
ከዚያ ውጪ ደግሞ፥ ከኣክስቷ ሞፊዳ ጋር መሆን ነው፤ ከኣክስቷ ጋር ለየት ያለ
ግንኙነት ነበራትና። ለምንኩስና ስላላት ከፍተኛ ጉጉት እንዲህ ትነግረን ነበር፦

[13] {ግብፆች አኅቴ ለማለት፥ «አም» የሚለውን ቃል ይጠቀሙበታል። ሆኖም ግን በእነርሱ ባሕል አኅቴ የሚባ
ለው ሰው የግድ የኣባት ወይም የእናት ወንድም መሆን አይጠበቅበትም። ማንኛውንም የሚያከብሩትን ሰው
"አም" ብለው ይጠራሉ። እኛ ጋሼ እንደምንለው ማለት ነው።}

ጠብቀው ብዙ መከራን የተቀበሉ ናቸው። ስለዚህ እግዚአብሔር የመከሩትን ክብር ሰጥታቸዋል። አሁን የቅድስት ዴምያናንና የአርባውን ደናግል በዓለ ንግሥ ለማክበር፥ ወደዚያ ልንሄድ ነው» አለችኝ። አብሬያችሁ መምጣት እፈልጋለሁ ስላት «በመጀመሪያ እናትሽን አስፈቅጂ» ስላለችኝ፥ እናቴን ስጠይቃት እኛ ስለምንፈልግሽ ከእነርሱ ጋር እንዳትሄጂ አለችኝ። ለአክስቴ ይህንኑ ስነግራት «መንኩሰሽ የገዳምሽ እመ ምኔት ትሆኖለሽ። ብዙ የመንፈስ ልጆች ካፈራሽ በኋላ ወደ እኛ ትመጫለሽ» አለችኝ።

ጠዋት ከዕንቅልፌ ስነቃ፥ ያየሁትን ሕልም ለወላጆቼ ነገርኋቸው። እነርሱም እየተገረሙ፥ ዛሬስ የቅድስት ዴምያና የሰማዕትነቷ በዓል ነው አሉኝ። እኔም «የአባቴ ገንዘብ ለገዳም መሥሪያ በቂ አይደለም። ስለዚህ አርሱን እንዳላስቸግረው፤ እግዚአብሔር ገንዘብ እንዲሰጠኝና መከሩላይያት የሚሰባሰቡበት፤ ትልቅ ገዳም እሠራ ዘንድ አማልጂኝ» ብዬ ወደ ሰማዕቷ ቅድስት ዴምያና ጸለይሁ።

<u>ሰማዕቱ አቡ ሰይፈ</u>ን፦ ዲዳን በሕልሜ ካየኋት ጊዜ ጀምሮ፥ እግዚአብሔር በቂ ገንዘብ እን ዲሰጠኝና፥ ገዳም መሥርቼ እንደ አርሱ ፈቃድ እንድኖር ይፈቅድልኝ ዘንድ፥ በአጽ ንዖት መጸለይ ቀጠልሁ። አንድ ምሽት፥ እያለቀስሁ ስጸልይ፤ አንድ መልከ መልካም የሆነ ብርሃናዊ ወጣት ወደ እኔ ዘንድ መጣ። «ምን ሆነሽ ነው የምታለቅሺው?» ሲለኝ፥ «አንተ ማንህ» አልሁት። እርሱም «ሰማዕቱ አቡ ሰይፊን ነኝ» ብሎ አንድ ሥዕል አሳይ ዞኝ ተሰወረ። ምንም እንኳን ዕድገቴ በሰንበት ት.ቤት ውስጥ ቢሆንም፤ ስለዚህ ሰማዕት ሰምቼም ሆነ አንብቤ አላውቅም። በማግስቱ፥ የቅድስት ድንግል ማርያም ቤተ ክርስቲያን ካህን ወደ ሆነው፤ ወደ አባ ጴጥሮስ ሄጀ የሆነውን ከነገርሁት በኋላ፥ «አቡ ሰይፊን የሚባል ሰማዕት አለ ወይ?» ብዬ ስጠይቀው፤ ጎዳር ጀሮ ቀን የሚነበበውን ስንክሳር ገልጦ ገድሉን አሰነበበኝ። ለመጀመሪያ ጊዜ የሰማሁት ታሪክም እጅግ አስደንቆኛል።

በሚቀጥለው ቀን ጸሎቴ፤ ሰማዕቱን ምን ማድረግ እንዳለብኝና ወደ ገዳምህም እንዴት እንደምሄድ፤ አንተ ምራኝ ብዬ ጠየቅሁ። ወዲያው ተገለጠልኝና ያንኑ በፊት የነገረኝን ደገመልኝ። አሁንም ወደ አባ ጴጥሮስ ሄጀ የሆነውን ነገርሁትና፤ ምናልባት የሰይጣን ፈተና እንዳይሆን? አልሁት። አርሱም ታገሺና አንድ ውጤት ታገኛ ለሽ አለኝ። አሁንም በሦስተኛው ቀን፤ የወታደር ልብስ ለብሶ መጣና «ካይሮ ለሚገ ኘው፥ በሰሜ የሚጠራ ገዳም አፈልግሻለሁ!» አለኝ። እየገረመኝ «ካይሮ ያለ ገዳም?!» ስለው «አዎን! ወሰጀ የት እንደሚገኝ አሳይሻለሁ። በገዳሙ ያሉ መነኮሳይያት ጥቂት ዘመዶቻቸው እዚያ በእንግድነት ስለሚያርፉ፥ አንቺን ማንም አያስተውልሽም። ጉዳዩ የሚመለከታቸው አንድ ወይ ሁለት መነኮሳይያት፥ የማን ዘመድ ነሽ? ብለው ይጠ ይቁሻል። አንቺ ግን መልስ ልትሰጫቸው አይገባሽም። በፈገግታ መልካም ፊት ብቻ አሳያቸው አለኝ። የሰይጣን ፈተና እንዳይሆን ፈርቻለሁና፥ በትእምርተ መስቀል አማ ትብልኝ ስለው አማተበልኝ። እጀ ላይም የሰጠኝን መስቀል ይዤው ይታየኛል፤ በጸ ሎቴ ሁሉ መስቀሉ አብሮኝ ነበር። አርሱም አይዞሽ አትፍሪ፤ ነይ እንሂድ» አለኝ።

መኝታ ቤቴ ውስጥ፤ በአንድ ጥግ በሎሌ፥ የጌታችን ሊየሱስ ክርስቶስ፣ የእ ናቱ ቅድስት ድንግል ማርያምና የሰማዕቱ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቅዱሳት ሥዕላት አሉኝ። በየዕለቱ ከፊታቸው ሻማ እያበራሁ፤ ጥቂት አበባዎችም አስቀምጣለሁ። የሴቶች ገዳም የት እንደሚገኝ ባላውቅም፤ የመመንኮስ ፍላጎቴ ግን ጽኑ ነበር። የተማርሁ በት ት.ቤት በካቶሊኮች የሚመራ ነበር። መምህራኑ የውጭ ዜጎች የሆኑ፤ የካቶሊክ መነኮሳይያት ናቸው። መምህራኖቼን፥ በእነርሱ ገዳም በምንኩስና እየኖርሁ፤ ንስሓ ዬንና ቅዱስ ምሥጢርን ግን፥ በእኔ የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን መፈጸም እችል እን ደሆነ ጠይቄአቸው፥ አይቻልም አሉኝ። በዚያን ጊዜ አባቴ ደግሞ፥ ከቤታችን ጣሪያ ላይ ለአንቺ የሚመጥን ገዳም (በአት) እሠራልሻለሁ ይለኝ ነበር።

የእኔ ምኞት ግን ራሱን የገዳሙን ሕይወት ማጣጣም ነው። «ዲዳ» እያልን የምንጠራት አክስቴ ሞፊዳም፥ ምኞቷ ልክ እንደ እኔው ነበር። እርሷ በዕድሜ ከእኔ ትንሽ ብትበልጥም፥ ጊዜያችንን እንደ ልጆች ተጫውተን ያሳለፍነው፤ ራሳችንን እያ መነኮሰን ነበር። ይህ ጨዋታችን የሚያጠይቀው መልኣካዊ የሆነውን የምንኩስና ሕይ ወት ምን ያህል እንናፍቅ እንደ ነበረ ነው። በመጀመሪያ ትልቋ ከመነኮሰች በኋላ፥ ትንሿ ደግሞ እንደምትከተል ተሰማምተናል። አክስቴ ዲዳ ውብ ልጅ ስለ ነበረች፤ እጇን ጠያቂ ሲመጣ ወላጆቿ አስገድደው ለእጮኛ ሰጧት። ሠርጓ ሲደርስ፥ በዋዜማው የእ መቤታችን ቅዱስ ሥዕል ፊት ቆማ፤ «እመቤቴ የብርሃን እናት! አስገድደው ሊድሩኝ ነው። እኔ የምፈልገው ደግሞ መንኩሴ መኖር ነው» ብላ ስታለቅስ፤ እመቤቴ ከሥ ዕሉ ላይ «ሂጂና እናትሽን፥ ልጅቷን ተያትና ወደ ገዳም ትግባ፤ እንቢ ካልሽ ግን ሰማያዊት ሙሽራ ሆና ወደ ልጄ ትሄዳለች፤ ተብለሻል በያት» አለቻት። ለእናቷ ይህ ንን መልእክት ስትነግራት፥ «ውሸትሽን ነው፤ እኔን በዚህ አስፈራርተሽ ገዳምሽ ለመ ግባት የፈጠርሽው መላ ነው» አለቻት። ዲዳ ምንም አማራጭ አልነበራትምና፤ ለሥ ርጉ ዝግጅት ከሚያደርጉት ዘመዶቿ ጋር ስትንጎዳጎድ፥ ድንገት ራሷን አመማት። ወደ ክፍሏ ልትገባ ስትል ወድቃ በዚያው ዕረፍቷ ሆነ።

እርሷ ስታርፍ፥ እኔ በጣም ትንሽ ነበርሁ። አብዝቼም አለቅስ ነበር። ነጫጭ ልብስ የለበሱ፤ እጅግ ብዙ ብርሃናውያን ደናግል በሕልሜ አየሁ። ራሳቸው ላይ አክሊል ያላቸው ሲሆን፥ በእጃቸው ደግሞ የአልማዝ መስቀል ይዘዋል። አክስቴ ዲዳም ከእነርሱ ጋር ነበረች። ባየሁት በጣም ተደሰትሁ። እርሷም «በእኔ ምክንያት እንዲህ ማልቀስ አግባብ ነውን? እኔ በገነት በመልካም ሥፍራ ነው ያለሁት። ደስተ ኛም ነኝ። ከምንም በላይ የሚያስደስተኝ ደግሞ፥ ጌታችን ሊየሱስ ክርስቶስ፥ በግርማ ሞገሱ ባለበት በዚያ መሆኔ ነው። አሁን ለአንቺ እንድንገለጥልሽ የፈቀደውም፥ እንደ ትረጋጊና ማልቀስሽን እንድታቆሚ ነው» አለችኝ።

አብረውሽ ያሉት ልጃገረዶች እነማን ናቸው? ስላት፥ «እነዚህ ሊመነኩሱ እየ ተመኙ፥ ሕልማቸው እውን ያልሆነላቸውና በምድራዊ ሕይወታቸው ንጽሕናቸውን

የነገሥታት ንግሥት የሆነች፥ የእምላካችን እናት፦ ወላጆቼ ለመመንኰስ ያለኝን ጽኑ ፍላጎት ሲያዩ፤ የዓሥራ አምስት ቀናት ሱባዔ ያዙ። ጊዜውም ከጾመ ነቢያት (የገና ጾም) ቀደም ብሎ ነበር። በየዕለቱ እያስቀደሱ አቀኑ በዘጠኝ ሰዓት ወደ ቤተ ይመሰላሉ። በሱባዔያቸው የመጨረሻ ዕለት፤ እናቴ ወደ ቤተ ክርስቲያን መሄድ ሰላልቻለች፥ ጸሎት ቤቷ ገብታ በጸሎትና በስግደት፤ እግዚአብሔር ለእኔ ያለውን ቦታ ነገር እንዲሰጠኝ በመጠየቅ ነበር ጊዜዋን ያሳለፈችው። ከዚያም ቤቱ በታላቅ ብርሃን ምላና ራእይ አየች። ሊቃነ መላእክት መጥተው የሆነ ነገር ይገነቡ ነበር። ምን እየሠራችሁ ነው? ብላ ስትጠይቃቸው «ለዓውደ ምሕረት መሥሪያ የሚሆን መሠረት እየገነባን ነው፤ የነገሥታት ንግሥት ወደዚህ ትመጣለችና ለእርሷ ነው» አሏት። ወዲያው ግንባታው ተጠናቀቀ፤ በወርቅ ያማረ ዙፋን አስቀመጡበት። ወላዲተ አምላክ ቅድስት ድንግል ማርያምም በቅዱሳን መላእክት ታጅባ መጥታ በዙፋኑ ላይ ተቀመጠች።

እናቴ ከእግሯ ሥር ሰግዳ «እመ ብርሃን! ክብርና ምስጋና ለኣንቺ ይሁን» አለቻት። እመቤታችንም «የመጀመሪያ ልጅሽን ስትወልጂ፤ <u>እርሷ የእኛ ናት</u> ብዬ የነገርሁሽን ረሳሽው? ለልጄ አጭቻታለሁና፥ ስለ እርሷ ምንም አያሳስብሽ፤ እንድትመነኵስ ፍቀጂላት፥ ልጄ ይጠብቃታል። አለበለዚያ ግን አሁኑኑ ወደ እኛ እንወስዳታለን ስትላት፤ እናቴ እሺ ድንግል እመቤቴ! እንደተናገርሽው ይሁን። ለቤተሰቤም ይህንኑ እነግራቸዋለሁ አለቻት። አባቴ ከቤተ ክርስቲያን እንደተመለሰ የሆነውን ስትነግረው፥ እሺ! አሁን ከቤታችን በላይ በኣቷን እንገነባላታለን፤ ወደ ሴቶች ገዳም ግን አትሄድም አለ። እንደ አለመታደል ሆኖ፤ በዚያ ዘመን የነበሩት ክርስቲያኖች፥ ስለ ገዳም ያላቸው ግንዛቤ የተሳሳተ በመሆኑ «ገዳም ገብቶና መንኵሶ የሚቀመጥ ሰው፤ ሠርቶ መብላት የማይችልና አካለ ጎደሎ ነው» ብለው ያስቡ ነበር።

መልካም ካህን የሆነው የንስሐ አባቴ አባ ማትያስ፥ እቤታችን መጥቶ ለአባቴ፤ የቤት ውስጥ (የከተማ) መነኵሴ መሆን ትርጉም የሌለው ነገር መሆኑን አሳመነው።[15] ከዚያም፥ «ለማንኛውም የኣንተ ልጅ በቅምጥል ያደገች ናትና፤ አንዴ ሄዳ አይታ፥ የኑሮውን አለመመቸት ስትረዳ፤ በሳምንቷ መጥተህ ውሰደኝ ማለቷ ስለማይቀር አትጨነቅ። መሄዷ በማንኛውም መንገድ ክፋት የለውምና ዝም ብለህ ላካት» አለው። የገዳምን ሕይወት ክብደትና ፈተናውን የሚያውቀው አባቴ ደስ ብሎት በካህኑ ሐሳብ ተስማማ።

በዚህ ሁኔታ ወደ ገዳም የመጣችው ፋውዜያ፤ በገድላቸውና በታሪካቸው የምታውቃቸውን ቅዱሳን፤ እንዲያማልዷትና መንገዷን እንዲያቀኑላት፤ እንዲያጽናኗትም እየተማጸነችና ከታላላቆቿ እግር ሥር ተቀምጣ በመማር፤ ሰማያዊ ምግቧን በመመገብ፤ የወጣኒ ኑሮዋን ቀጠለች። ታላላቆቿም በበኩላቸው እርዳታዋን ሲሹ ወደ

[15] አባ ማትያስ የአል-ኮሽ ሰው ነው። በቅድስናው የታወቀና፤ አንድ ችግር ሲከሰት ለብቻው ተወስኖ የሦስት ቀናት ሱባዔ የመያዝ ልምድ ያለው ነው። ለጥያቄውም መልካም ምላሽ ያገኛል። የቅብጥ ቤተ ክርስቲያን ሐምሌ ፲፮ ቀን ታዘክረዋለች።

በፈረሱ ጀርባ ላይ ተቀምጠው፥ ደቂቃ ባልሞላ ጊዜ ውስጥ በገዳሙ ሕንፃ ሁለተኛ ፎቅ ላይ አረፍን። ሁለት መነኰሳይያት «ቆንጅዬ! የማን ዘመድ ነሽ?» አሉኝ። በሰማሁት እንደታዘዝሁት፤ ፈገግታ ብቻ አሳይቼ ዝም አልሁ። እርሱ ግን ለእነርሱ አልታያቸውም። ገዳሜን አየሽው? ሲለኝ፥ አዎ ግን እንዴት ነው ወደዚህ መምጣት የምችለው? አልሁት። ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ መንገዱን ያዘጋጅልሻል፥ ብሎ ጊቢው ንና አካባቢውን፤ ሄርማል ሆስፒታልንና የባቡር ጣቢያውን አዘዋውሮ ካሳየኝ በኋላ፥ ወደ ወላጆቼ ቤት ወደ ጊርጋ መለሰኝ።

የእግዚአብሔር ፈቃድ ሆኖ፤ እማሆይ ማሪያ የተባለች መነኵሲት ወንድሟን ለመጠየቅ፤ ከካይሮው አ.ሰ.ቤ.ገ. በከተማችን አካባቢ ወደሚገኘው፥ «ሼይኽ ዓለም» ወደ ተባለ መንደር መጣች። ጊርጋ ከናይል በስተ ምዕራብ፥ ሼይኽ ዓለም ደግሞ፥ በስተ ምሥራቅ ያሉ ቀበሌዎች ናቸው። «የነቢዩ ዮናስ መታሰቢያ የሆነውን፤ የነነዌ ጾም ያስቀደሰችውም በእኛ አጥቢያ ስለ ነበር፥ ጓደኛዬ ወደ እኔ መጥታ፥ ከቅዱስ መርቆሬዎስ ገዳም፤ እንዲት መነኰሲት መጥታለች አለችኝ። እርሷን ለማግኘት ከነበረኝ ጽኑ ፍላጎት የተነሣ፤ ወዲያው ሄጀ ተዋውቄ፥ ሦስቱን የጾም ቀናትም በእኛ ቤት እንድታሳልፍ ጋበዝኋት። ጊዜኣችንንም ሁሉ ያሳለፍነው፤ በእኔ መኝታ ቤት ውስጥ ለብቻችን ሆነን ነው። በዚህ ጊዜ የልቤን ምኞት ነግሬ ጸልዩልኝ አልኋት። ጾመ ነነዌ ተፈጽሞ፥ በዕለተ ሐሙስ፤ ከኣባቴ ጋር ቁጭ ብለው ሲነጋገሩ፥ ስለ ገዳሙ ሁኔታ ጠየቃት። አጠያየቁ፥ በብዙ ነገሮች ሲጋት ስላደረበት፥ በተለይ ወደዚያ ገዳም እንዴት ሄድ ለማድረግ ምክንያት ያገኘ ዘንድ ነበር።

በጥቂት ቀናት ውስጥ፥ እማሆይ ማሪያ የቀዶ ሕክምና ለማድረግ ሐኪም ቤት ገባች። ልጠይቃት ሰሄድም፥ ተሸኚት ወደ ገዳሙ ስትመለስ፥ የገዳሙ እመምኔት ለሆነችው ለእማሆይ ኬርያ ዋስፍ[14] (Mother Cereia Wassef) የእኔን ጉዳይ እንደምታሳስብልኝና በጎረቤት አድራሻ ደብዳቤ እንደምትልክ ቃል ገባችልኝ። ወደ ገዳሚ እንደ ተመለሰች፤ በገባችልኝ ቃል መሠረት ደብዳቤዋ በጓደኛዬ በኩል ደረሰኝ። አንድ ቀን ግን ደብዳቤው በቀጥታ በእኛ አድራሻ መጣና አባቴ እጅ ገባ። ሲያነበው በባቡር ተሰፍረሽ ነይና «ጊዛ» ጣቢያ ስትደርሺ ውረጂ። እኔ እዚያ እጠብቅሻለሁ የሚል መልእክት ነበር የተላከልኝ። አባቴ በፈገግታ ካስተዋለኝ በኋላ፥ «እናትና አባትሽን ማሳዘን አግባብ ነውን? ልጃቸው ጠፍታ ሄደች ሲባል፤ የኣካባቢው ሰውስ ምን ይለናል? ባይሆን በት ዕግሥት በጸምና በጸሎት የእግዚአብሔርን ፈቃድ ጠይቂ። የእርሱ ፈቃድ ከሆነ፥ እኔ ራሴ ይገፍሽ እሄዳለሁ እንጂ አንቺ ባሰብሽው መንገድ ግን አይሆንም አለኝ።

[14] እማሆይ ኬርያ ዋስፍ የታህታ ባኒ ሐርብ ተወላጅ ናት። ወደ ገዳም የገባችው በ፲፰፻፲፮ ዓ.ም. ሲሆን፤ በዚያው ዓመት በኣባ ጳውሎስ (Buolos) አል-ባራሙሲ እጅ ምንኵስና ተቀበለች። በ፲፱፻፳፩ ዓ.ም. የገዳሙ እመምኔት ሆና ተሹማለች። መስከረም ፲፮ ቀን ፲፱፻፶፩ ዓ.ም. ከምሽቱ በ፫ ሰዓት ዕረፍቷ ሆነ። መንፈሳዊ ሕይወቷ እጅግ የጠነከረ በመሆኑና፥ ብሉይና ሐዲስን በቃልዋ በማጥናቷ ብዙዓን አባቶች «ቅዱስ ጳውሎስ» የሚል ቅጽል ስም አውጥተውላታል። አቡ ሰይፊንም ብዙ ጊዜ ይገለጥላት የነበረ ሲሆን፥ ከዕረፍቷ በኋላ እርሷም ለባማፍ ጌራኒ (እመምኔት በሆነች ጊዜ) እየተገለጠች ታጽናናት ነበር።

እርሷ ይመጣሉ። በዚህ ጊዜ ነው፥ ወደዚህ ገዳም ለመምጣት የረዳትን «ወንጌሉ ዘወርቅ» በሚል ቅጽል የሚታወቀውን፤ ቅዱስ ዮሐንስን እንዴት እንዳወቀችው የነገረችን።

ቅዱስ ዮሐንስ-ወንጌሉ ዘወርቅ፦ አንድ ቀን ቁጭ ብዬ፥ ቅዱስ ዮሐንስ «ወንጌሉ ዘወርቅ»፥ የተባለውን አባት ታሪክ የያዘ መጽሐፍ እያነበብሁ ነበር። ዕለቱም የዕረፍቱ መታሰቢያ የሚከበርበት ነው። እኔም ታሪኩን እያነበብሁ ሳለ፥ መጽሐፉ የተጋነነ ነገር እንዳለው አስብ ነበር። ወዲያው በአንድ እጁ መስቀል፥ በሌላ እጁ የወርቅ መጽሐፍ ቅዱስ ይዞ ተገለጠልኝ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ፤ ወደ ምንኩስና ሕይወት ለመግባት መንገዱን ያቀልልኝ ዘንድ በጸሎት እማጸነው ነበር። አንድ ቀን እንዲህ አለኝ፦ «አታስቢ! አሁን ከአባትሽና እናትሽ ጋር ነበርሁ። እንዲረጋጉና እንዲፈቅዱልሽ አድርጌአቸዋለሁ» አለኝ። ወዲያው ወደ ክፍላቸው ስገባ፥ ሁለቱም በፈገግታ ተቀበሉኝና «እንድትሄጂ ፈቅደንልሻል» አሉኝ። ማን እሺ እንዳሉኖችሁ አውቃለሁ ስላቸው «አዎን፤ ቅዱስ ዮሐንስ ወንጌሉ ዘወርቅ ተገልጦልን ነበር» አሉኝ።

ጥር ፳፩[16] ቀን የሚነበበው የስንክሳር ክፍል፥ ይህ ቀን የቅዱስ ዮሐንስ ወንጌሉ ዘወርቅ፤ ቤተ ክርስቲያኑ የከበረችበትና ሥጋው ወደ ሮሜ የፈለሰበት መሆኑን ይገልጻልል። እንዲሁም ሐምሌ ፲፯[17] ቀን፥ የቅዱስ ዮሐንስ ወንጌሉ ዘወርቅ ዕረፍቱ መሆኑ ተጽፏል፦

ይህም ቅዱስ ከሮሜ አገር ነበር። አባቱም አጥራብዮስ የሚባል ባለ ጠጋ ነው። የእናቱም ስም ብዱራ ይባላል። እንዲማርም ለመምህር ሰጡት። ቅዱሳት መጻሕፍትንም ተማረ። ከዚህም በኋላ፥ ገበታው የወርቅ የሆነ ወንጌልን ያሠራለት ዘንድ አባቱን ለመነው። አባቱም እንደ ፈለገው አሠራለት። ሁል ጊዜም ያነበው ነበር። በሚያነብ ጊዜም አባቱና እናቱ ደስ ይላቸው ነበር። በዚያም ወራት ወደ ኢየሩሳሌም የሚጓዝ መነኮሴ ወደ እነርሱ መጣ። በእነርሱም ዘንድ አደረ። ከቅዱስ ዮሐንስም ጋር ተነጋግሮ የምንኩስናን ሥራ አመሰገነለት። ይህን ዓለም እስከ ናቀና እንደ እርሱ መነኰሰ ይሆን ዘንድ እስከ ወደደ ድረስ ልቡን ማረከው።

ያን ጊዜም ያ መነኰሰ ወደ ኢየሩሳሌም ተጓዘ። ሁለተኛም ተመልሶ እንደ ልማዱ በእነርሱ ዘንድ አደረ። ቅዱስ ዮሐንስም መነኰሴው ወደ ገዳሙ ይወስደው ዘንድ ፈለገ። መነኰሴውም አባትህን እፈራዋለሁ ልወስድህ አይቻለኝም አለው። ቅዱስ ዮሐንስም ከእርሱ ጋር እንዲወስደውና ነፍሱን እንዲያድን አማለው። ከዚህም በኋላ በሥውር ወሰደው። በመርከብም ተጭነው ያ መነኰስ ወደሚኖርበት ገዳም ደረሱ። የገዳሙም አበምኔት የወጣቱን የዮሐንስን መልኩን አይቶ አደነቀ።

ከዚህ በኋላ ከጸም ከትጋትና ከኃዘን የተነሣ ሥጋው ደርቆ አጥንቶቹ እስከሚታዩ ድረስ በብዙ ተጋድሎ ተጸመደ። አበምኔቱም ልጄ ሆይ! ለሰውነትህ እዘን፣ ድካምህንም ቀንስ። መነኰሳቱም ሁሉ እንደሚሠሩት ሆነህ ሥራ፥ እያለ ያጽናናውና ይመክረው ነበር። በዚህ ተጋድሎም ሰባት ዓመት በሆነው ጊዜ፥ ከእነርሱ በረከትን ትቀበል ዘንድ ከመሞትህ በፊት ወደ አባትህና እናትህ ሂድ፥ የሚል ራእይ አየ። ይህንንም ራእይ በሦስት ሌሊቶች ውስጥ አየ። ለአበምኔቱም እንዴት እንዳየ ነገረው። አበምኔቱም ይህ ራእይ ከእግዚአብሔር ዘንድ

[16] {መጽሐፈ ስንክሳር ከመስከረም/ ትግድ/ ኢስ /፲፱፻፹ ዓም/ ገጽ ፭፻፶፯}
[17] {መጽሐፈ ስንክሳር ከመጋቢት ፳ / ትግድ/ ኢስ /፲፱፻፹ ዓም/ ገጽ ፭፻፹፫}

ስለ ሆነ ልትሄድ ይገባሃል አለው። ከገዳሙም በወጣ ጊዜ፥ አንድ ምስኪን ሰው ጨርቅ ለብሶ አገኘ። የእርሱንም ልብስ ሰጥቶት ጨርቁን ወሰደ። ወደ አባቱ ቤትም በደረሰ ጊዜ በትንሽ ጎጆ ውስጥ በአባቱ ደጅ በጾም በጸሎትና በስግደት እየተጋደለ፣ ባሮች ከአባቱ ማዕድ የሚጥሉለትን ፍርፋሪ እየተመገበ ሰባት ዓመት ኖረ።

እናቱም በአንጻሩ ስታልፍ የሚከረፋ ሽታው ያስጨንቃት ነበር። ዕረፍቱም በቀረበ ጊዜ፥ የአግዚአብሔር መልኣክ ከሰባት ቀን በኋላ ከዚህ ዓለም ትወጣለህ ብሎ ነገረው። ያን ጊዜም ወደ እናቱ ልኮ፣ ልትሰማ ወደ እርሱ መጣች። ልጅዋም እንደ ሆነ ፈጥኖ አልነገራትም። ነገር ግን በዚያች በታናሽ ማደሪያ ውስጥ በላዩ ባለ ጨርቅ እንድትቀብረው የለበሰውንም ጨርቅ እንዳትለውጥ አማላት። ከዚህም በኋላ ያንን የወርቅ ወንጌል ሰጣት፤ እንዲህም አላት። ይህን መጽሐፍ አንብቡ፥ እኔንም አስቡኝ። አባቱም በመጣ ጊዜ፥ ያንን የወርቅ ወንጌል አሳየችው። እርሱም ለልጁ ያሠራለት ወንጌል እንደ ሆነ አወቀ። አባቱና እናቱም ወደ እርሱ ሄደው ስለ ልጃቸው ጠየቁት። እርሱም ከዚህ ጨርቅና ከዚህ ትንሽ ማደሪያዬ ውስጥ በቀር፥ በሌላ እንዳትቀብሩኝ ማሉልኝ አላቸው።

በአማላቸው ጊዜ እርሱ ልጃቸው እንደ ሆነ ነገራቸው። ያን ጊዜም ጮኹ፣ መሪር ልቅሶንም አለቀሱ። የሮሜ ከተማ ሽማግሌዎችና ሕዝቡ ሁሉ ተሰበሰቡ። ሰባቱ ቀንም ሲፈጸም ቅዱስ ዮሐንስ አረፈ። እናቱም መሓላዋን ረስታ አስቀድማ ለሠርጉ ያዘጋጀቻቸውን ያማሩ ልብሶች አውጥታ ገነዘችው። በዚያችም ጊዜ ታመመች። አባቱ ግን መሓላውን አስታውሶ እነዚያን ያማሩ ልብሶች አስወገደ። በጨርቆቹም ገነዙት። በዚያ በትንሹ ማደሪያም ውስጥ ቀበሩት። ከሥጋውም በሽተኞች የሚፈወሱበት ታላቅ ድኅነት ተገኘ። ከዚህም በኋላ፥ በስሙ ያማረች ቤተ ክርስቲያን ሠርተው ሥጋውን በውስጧ አኖሩ። ከእርሱም ታላላቅ ድንቆችና ተአምራቶች ተገለጡ። ለእግዚአብሔር ምስጋና ይሁን፥ እኛንም በጸሎቱ ጎይል ይማረን፥ በረከቱም ከእኛ ጋራ ትኑር፥ ለዘላለሙ አሜን።

ወደ ቀደመ ነገራችን እንመለስና፥ እግዚአብሔር በፈቀደበት ቀን ደግሞ፥ እማሆይ ማሪያ ወደ ጊርጋ ሰለ መጣች፥ አብሬያት እንድሄድ ተስማማን። በጉዞዬ ዋዜማ፥ የአባቴ ወንድም የሆነ፥ ተውፊቅ የተባለ አጎቴ፤ ወሬውን ሰምቶ፥ እየተበሳጨ ወደ ቤታችን መጣ። አባቴንም «እንዴት እንድትሄድ ትፈቅድላታለህ? በፍጹም ልትሄድ አትችልም። እኔ ከበሩ አላስወጣትም» ብሎ ዛተ። ከዚያም ወንበር ሰቡ፥ በሩ አጠገብ ተቀመጠ። ልክ የመውጫዬ ሰዓት ሲደርስ ግን፥ አባድ ዕንቅልፍ ስለያዘው፤ የሚደረገውን ለማወቅ አልቻለም። በዚህ ሁኔታ፥ ያለምንም ችግር ወጥቼ፤ ከእማሆይ ማሪያ ጋር ወደ ባቡር ጣብያ ሄድሁ። አባቴም ተከትሎኝ ስለ ነበር፥ ትኬታችንን ቆርጠ ሸኘን። አጎቴ ሐሳቡቅልፉ ሲነቃ፤ ሊያስቆመኝ ፈጥኖ ወደ ባቡር ጣቢያው ሲመጣ፥ ባቡሩ ጉዞ ጀምሯል።

በዚህ ሁኔታ ነበር፥ ፋውዜያ ሚያዝያ ፰ ቀን ፲፱፻፸፯ ዓ.ም.፤ መልኣካዊ ሕይወቷን የምታጣጥምበትን ኑሮ፤ አንድ ብላ ለመጀመር ወደ ካይሮ ያቀናችው። የልቧ መሻት ተሟልቶላት፤ እግሯ ወደ ገዳሙ ከገባበት ጊዜ ጀምሮ፤ ለፈጣሪዋ ያላት ፍቅር መገለጥ ጀመረ። በተጋድሎ ጽናትም ወደ ብቃት ደረጃ ደረሰች።

ለመሆኑ ጠላት ዲያብሎስ ወጣት ፋውዜያን ዝም ብሎ ያያት ይሆንን? ሰማ ያዊውን መንግሥት የሚናፍቀውን ልቧን ያለፈተና ይተወው ይሆንን? በወጣት ዕድሜዋ ገዳማዊ ሕይወትን በምን ሁኔታ ትቋቋመው ይሆን? ለሌሎች የመታዘዝና የማ ገልገል፣ ለፈጣሪዋ እንደ ገባችው ቃል ሆና የመገኘት፣ በበኣት ተወስኖ የመጸለይና ከቅዱሳኑ ጋር አንድነቷን የማጠንከር፤ . . . በተለይ ደግሞ፥ በገዳሙ በምንኩስና እግዚአብሔርን እንድታገለግል የተዘጋጀችለት የኣቡ ሰይፊን ተራዳኢነትስ? በሚቀጥሉት ምዕራፎች የምንመለከታቸውና መልስ የምንሰጥባቸው ጥያቄዎች ናቸው።

ምዕራፍ ሁለት

የመልኣካዊ ሕይወት ውጣኔ፣ ገድል -በገዳማዊ ሕይወት።

እናንተ የተወደዳችሁ ደናግል ሆይ! የቅድስተ ቅዱሳን የእመቤታችን ድንግል ማርያም ልጆች ትሆኑ ዘንድ፤ የንጽሕናን ሕይወት ውደዱት።